<<ማኅበረ ቅዱሳን>> እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜ አግኝቷል።



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በልማት ተቋማት አስተዳደር በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ


**፳፮ኛ ዓመት ቁጥር ፩**
**መስከረም ፳፻፲፩ ዓ.ም.**


# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ


ም/ዋና አዘጋጅ
ዲያቆን አሻግሬ አምጤ
አድራሻ፡-የካ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 01/02 የቤት ቍጥር 521/522
ስልክ +251- 911361580
ከፍተኛ ሪፖርተር
ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን
ጸሐፊና ሌይ አውት ዲዛይነር
ገነት ታደሰ
አሳታሚ
በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት
አ.አ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06


## ማውጫ


መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን
በአዲስ ዓመት አዲስ ሰውነት ................................ ፪
ዐውደ ስብከት
"በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ" (ኢዩ.፪÷፲፪).........፬
ትምህርተ ሃይማኖት
ተስፋ አያሳፍርም (ሮሜ ፰፥፰) ................................ ፯
ዐብይ ጉዳይ
ዘመኑ ለጽድቅ የምንበቃበትን ተግባር የምንፈጽምበትይሁን
..........................................................................፲፭
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
"መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን
አትርሱ"(ዕብ.፲፫፥፲፮)........................................ ፲፬
እናስተዋውቃችሁ
ዚኖቢስና ዚኖቢያ............................................ ፲፯
የነገዋ ቤተ ክርስቲያን
ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ሕመምተኞች
ያላት አስተዋጽኦ..........................................፲፱
ኪነ ጥበብ
ጸጸት......................................................፳፪
ጥያቄዎቻችሁ መልስ
...........................................................፳፯



የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
ስልክ +251-118-124222
ፖ. ሣ. ቍ.80078
ኢ.ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት
ስልክ +251-962171717
የልማት ተቋማት ሽያጭና ስርጭት መምሪያ
ስልክ 0111540484/0111246184/0944259014
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
0111246184/0913296480

# በአዲስ ዓመት አዲስ ሰውነት

አዲስ ዓመት ሲመጣ አዲስ ሰው ለመሆን ተዘጋጅቶ መጠበቅ ከመንፈሳውያን ሁሉ የሚጠበቅ በጎ ተግባር ነው። ሰዎች ካልተቀየርን የዘመኑ መቀየር ብቻውን ጠቀሜታ የሌለው መሆኑን ተረድተን በዘመኑ ለመጠቀም መወሰን ይኖርብናል። ከዘመን ዘመን ስለተሸጋገርን ብቻ የምንደሰት ከሆነ የተፈጠርንበት ዓላማ፣ የመኖራችንም ትርጉም አልገባንም ማለት ነው። አዲስ ዘመን ሲመጣ ሕይወትን ለመቀደስ ካልተጠቀምንበት ተፈጠሩ ሞቱ መባል ብቻ ይሆናል። ነቢዩ ዳዋት "በቸርነትህ ዓመታትን ታቀዳጃለህ፣ ምድረ በዳዎችም ጠልን ይጠግባሉ፤ የምድረ በዳ ተራሮችም ይረካሉ፤ ኮረብቶችም በደስታ ይታጠቃሉ"(መዝ.፷፬፥፲፩-፲፪) በማለት የተናገረው በኃጢአት ባሕር ሲዋኝ የኖረውን፣ ከእግዚአብሔር ተለይቶ፣ ከመጥፎ ነገር ጋር ተባብሮ ይኖር የነበረውን መልካም እንዲያስብ፣ ሟች መሆኑንም እንዲገነዘብ በማድረግ የጽድቅን ጎዳና እንዲከተል ልቡናውን የቀሰቀሰው እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ለመመስከር ነው።

በአንጻሩ አንዳንድ ሰዎች አምላካቸው ረጅም ዕድሜ ሲሰጣቸው የዕድሜያቸውን መርዘም ምክንያት በደንብ ባለመረዳት በኃጢአት ላይ ኃጢአት ሲሠሩ ይታያሉ። ሲሠሩት የሚጣፍጣቸው ኃጢአት ቆይቶ መከራ እንደሚያመጣ ማሰብ አይፈልጉም። ዘመናቸውን ሳያልፍ እንጠቀምበት ቢሉም ኃጢአት ሠርተው ሳይጠግቡ በመከራ መቀሰፋቸው አይገለጥላቸውም። አዲስ ሰው ለመሆን መሠራት የሚገባውም "ኃጥእን ከፍ ከፍ ብሎ እንደ ሊባኖስ ዝግባም ለምልሞ አየሁት፤ ብመለስ ግን የነበረበትን ቦታ አላገኘሁትም" በማለት ነቢዩ ዳዊት የተናገረው እንዳይፈጸምብን ነው (መዝ.፴፮፥ ፴፭)። ዘመናችን ከመከራ ለመጠበቅ ወደ አምላካችን የምንቀርብበት እንጂ ለበለጠ መከራ የሚዳርገንን መጥፎ ድርጊት የምንፈጽምበት መሆን የለበትም። የነበረው በቅጽበት እንዳልነበር ሲሆን እያየን፣ ከእኛ ወዲያ ሥልጣኔ ይሉ የነበሩ መታሰቢያቸው ሊጠፋ ተቃርቦ እየተመለከትን አዲሱን ዓመት በኃጢአት እንደተጨማለቅን መጠበቅ እና በኃጢአት ላይ ኃጢአት ለመሥራት ዕቅድ ማውጣት በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ እንዲፈረድብን ወደን ፈቅደን በመግባታችን ነው።

አምላካችን እግዚአብሔር ወደ አዲስ ዓመት የሚያሸጋግረን አዲስ ሰው እንድንሆን ነው። በኃጢአት ላይ ኃጢአት ለመሥራት ባለመጥገባችን ዓለማችንን በየቦታው ጦርነት፣ በሽታ፣ ጎርፍ፣ ወረርሽኝ እያስጨነቃት ነው። እንዲህ ዓይነት ችግር ሲፈጠር ጣትን ወደ ሌላ ከመጠቆም ይልቅ ራስን በመመርመር የችግሩ አካል መሆን አለመሆንን ማየት ይገባል። ሁላችንም ችግሩ የሌሎች መሆኑን እንናገራለን እንጂ የችግሩ ምክንያት "እኔ እሆን ?" ብለን ራሳችንን ጠይቀን አናውቅም። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን "እውነት እውነት እላችኋለሁ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል" ባላቸው ጊዜ እኔ እሆን? አሉ እንጂ ሌባ መሆኑን የሚያውቁት ይሁዳ ይሆናል አላሉም። ለአምላካቸው መሰቀል ምክንያት አለመሆናቸውን እያወቁ እኔ እሆን? ብለው ራሳቸውን በመጠየቃቸው አምላካቸው ለሞቱ ምክንያት የሆነውን ይሁዳን አሳያቸው።

በቀጣዩ አዲስ ዓመት አዲስ ሰው ለመሆን የሚያግዙንን መልካም ተግባራት ማከናወን እንደሚኖርብን ማቀድ እንጂ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ለመደረብ መዘጋጀት የለብንም። ዘመናችንን የተባረከ የሚያደርገው አእምሯችንን ንጹሕ የሚያደርግ ተግባር መፈጸም ነው። ለዚህም ቀዳሚው ተግባር ከአጥፊዎችና ከጥፋታቸው ጋር አለመተባበር ነው። ከጥፋት አለመተባበር ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት እና የአገር መገለጫ የሆኑ ቅርሶቻችን እንዳይወድሙ መጠበቅም ይኖርብናል። የኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆኑ የሌሎች ወገኖቻችን የእምነት ተቋማትም አደጋ እንዳይደርስባቸው የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርብናል። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር "ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" ተብሎ የተነገረንን በተግባር ለመግለጥ ያግዘናል። በጦርነቱ ምክንያት በየቦታው ቅርሶቻችን እየወደሙ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በመተባበር ጥበቃ

ልናደርግላቸው ይገባል:: ግንባር ላይ የተሰለፉ ወገኖችም ቅርሶች የራሳቸው ንብረት መሆናቸውን ተረድተው በጦርነቱ ምክንያት እንዳይወድሙ አስፈላጊውን ጥበቃ ሊያደርጉላቸው ይገባል::

የአገራችን የሆነው ሁሉ የእኛ በመሆኑ ክርስቲያኖች የእኛ የእምነት ተቋም ብቻ ይጠበቅ አንልም:: የአገራችን የሆነው ሁሉ ተጠብቆ ለትውልድ እንዲሸጋገር ማደረግ የሁላችን ኃላፊነት ነው:: ሁላችንም ሰላማውያን ለመሆን ካልተዘጋጀን በተወሰኑ ሰዎች ሰላማውያን መሆን አገር ሰላማዊ አይሆንም:: አገር ሰላማዊ የምትሆነው፣ አምላካችን ጸሎታችንን የሚቀበለው በአዲሱ ዓመት ከሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር ቃል ከመግባት ዐልፈን ተግባራዊ ሥራ ስንፈጽም፣ አዲስ ሰው ለመሆንም ስንዘጋጅ ነው:: ሌላውን አጥፍተው ለመኖር መሞከር የሚፈልጉ ወገኖች የደረሰባቸውን መከራ እያየን ነው:: ከተከሠተው የበለጠ መከራ እንዳይመጣብንና የመጣውም መከራ በቶሎ እንዲቆም በፍጹም ልባችን ወደ አምላካችን በመመለስ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ተግባር ለመፈጸም መዘጋጀት ይኖርብናል:: አምላካችን ቤተ አይሁድን "ኑ እና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ቢሆን እንደ በረዶ አነጻዋለሁ፤ እንደደምም ቢቀላ እንደ ባዘቶ አጠራዋለሁ:: እሺ ብትሉና ብትሰሙኝ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤እንቢ ብትሉና ባትሰሙኝ

ባትሰውኝ ግን ሰይፍ ትበላችኋለች፤ የእግዚአብሔር ቃል ይህን ተናግሯል"(ኢሳ.፩፥፲፰) በማለት የተናገራቸው ይህን ዘመን የሚመለከት ነው:: በቅዱሳን የተነገረውን ቃል ሰምተን ባንታዘዝ የሚገጥመን መከራ ነግሮናል:: ጥፋታችንን አምነን ወደ እርሱ ብንመለስ ደግሞ የምናገኘውን በረከት አሳውቆናል:: አዲስ ሰው ለመሆን የሚገባንም የእግዚአብሔር ሰይፍ እንዳይበላን ነው:: የእግዚአብሔር ሰይፍ የሚባለው ጦርነት፣ በሽታ፣ ወረርሽኝ፣ ጎርፍ፣ ማዕበል እና የመሬት መንቀጥቀጥ ነው::

አምላካችን እግዚአብሔር ኑና እንዋቀስ በማለት የተናገረው እርሱ ጥፋት ኖሮበት ሳይሆን እኛን በፍቅር ሊስበን ፈልጎ ነው:: አምላካችን እንዳንጠፋበት ፈልጎ በፍቅር ሲጠራን እኛ ደግሞ በቁጣ ከሚመጣ መቅሰፍት ለመዳን የፍቅር ጥሪውን ተቀብለን በንስሓ ወደ እርሱ መቅረብ አለብን:: ጥሪውን አልሰማ ብለን በኃጢአት የምንቀጥል ከሆነ መከራውን ወደ ራሳችን እየጋበዝን፣ የሚመጣብንን መቅሰፍት እያፋጠንን፣ የሞት መንገዳችንንም እየሠራን እንጂ ለጽድቅ የሚያበቃንን እየፈጸምን አይደለም:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ "ዝሙትንና ምኞትን፣ ፥ስካርን እና ወድቆ ማደርን ያለልክ መጠጣትንና ጣዖት ማምለክን ያደረጋችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃችኋልና:: እንግዲህ ወደዚህ ሥራ እንዳትሮጡ ዕወቁ፤ ከዚች ጎዳናና መጠን ከሌለው ከዚያ ሥራም ተለዩ" (፩ኛ ጴጥ.፬፥ ፫-፬) በማለት የተናገረው በእንደዚህ ዓይነት የመከራ ዘመን ወደ አምላካችን ብንመለስ ከደረሰብን መከራ በኃጢአት ከመሞትም እንድናለን::

ራሳችንን መጠበቅ የሚኖርብንም አካላችን ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ብቻ ሳይሆን ኃጢአት ሠርተን ከአምላካችን ተጣልተን እንዳንቀር ጭምር ነው:: ዝሙት፣ ስካር፣ ወድቆ ማደር የአሕዛብ ፈቃድ በመሆኑ ሐዋርያው "የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት ዘመን ይበቃችኋል" በማለት ነገረን:: አልመለስ ካልንም የሚደርስብንን መከራ አስታወቀን:: ከክፉ ርቀን መልካም ነገር የምናደርገው አምልኮ የምንፈጽምባቸውን አብያተ ክርስቲያን በመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ችግር የገጠማቸው እንዲጽናኑ የምንችለውን ሁሉ በመሥራት ጭምር ነው:: ታሪክ ሠርተን ማለፍ፣ እግዚአብሔርንም የሚያስደስት ተግባር መፈጸም ሲገባን አባቶቻችን ለዘመናት ከውጭ ወራሪ ጠብቀው ያቆዩዋቸው ቅርሶች ሲወድሙ ቆመን ማየት ወይም እንዲጠፉ መተባበር ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ቀጣዩንምት ትውልድ መግደል ነው:: የራሳችንን ሕይወት ከመቀደስ በተጨማሪ አገልጋይ ሊቃውንትን እና አብያተ ክርስቲያናትን ጠብቀን ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ማድረግ በዚህ ዘመን ከምንገኝ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚጠበቅ ኃላፊነት መሆኑን መግለጥ እንወዳለን::✤

# "በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ"

(ኢዩ. ፪÷፲፪)

ዲ/ን ተስፋዬ ምትኩ

ቸርነት፣ ደግነት፣ ምሕረትና ይቅር ባይነት የባሕርይ ገንዘቦቹ የሆኑት አምላካችን እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠራቸው የሰው ልጆች ከመንገዱ በመውጣት በጠላት ወጥመድ ተይዘው እንዳይቀሩ "ወደ እኔ ተመለሱ" እያለ ዘወትር ይጠራቸዋል፡፡ ይህ ጥሪ የንስሓ ጥሪ ነው፡፡ ንስሓ መጸጸት፣ መቆጨት፣ በሠሩት ክፉ ተግባር ማዘን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ንስሓ በሙሉ ልብ መመለስንና መለወጥን ያመለክታል፡፡ የሰው ልጅ ድካም የሚስማማውን ሥጋ እንደ መልበሱ ይደክማል፤ ይዝላልም፡፡ ከእውነት መንገድ፣ ከጽድቅ ሕይወት ወጥቶ ይስታል፡፡ ይሁን እንጂ የሚያስብ አእምሮና የሚያመዛዝን ሕሊና ያለው ፍጡር በመሆኑ የሠራውን ስሕተት አስተውሎ ይጸጸታል፡፡ ጸጸቱ የአሳብ ለውጥ መኖሩን ያመለክታል፡፡ ይህ የአሳብ ለውጥ ብቻ መፍትሔ አይሆንምና በተግባር መገለጥ አለበት፡፡ በአሳብም በተግባርም መለወጥ ማለት የንስሓ ጥሪን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

ጠቅለል አድርገን ስንመለከት ንስሓ እከብር ባይ ልቡና የሚያሳስበንን ሥጋዊ ፍላጎት ተከትለን፣ ስላጠፋነው ጥፋት፣ ስለበደልነውም በደል ምሕረትና ይቅርታ የምንጠይቅበት ለኃጢአትና ለጥፋት የጋበዘንን ሥጋችንን የምንገሥጽበት እና የምንቀጣበት፣ የእግዚአብሔርንም ቸርነት ደጅ የምንጠናበት ሥርዓት ነው፡፡ ስለዚህ ንስሓን ስናስብ ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን መዘንጋት የለብንም፡፡ እነሱም፡- መናዘዝ፣ የሚሰጠንን ቀኖና መፈጸምና፣ ለኃጢአታችን ሥርየት የተሠዋልንን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቀበል የሚሉት ናቸው፡፡

### ፩. ኃጢአትን መናዘዝ

የራስን ጥፋት አውቆ ለእግዚአብሔርም ለሰውም መናዘዝ የንስሓ የመጀመሪያው ደረጃ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አስተምህሮ መናዘዝ ስንል ሰው በአሳብ፣ በንግግር እና በተግባር በፈጸመው ኃጢአት ተጸጽቶ "እባክህ ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቀኝ" ብሎ ጥፋቱን ለካህን ዘርዝሮ የሚናገርበት ሥርዓት ነው፡፡ አንድን ተነሳሒ እና ካህንን የንስሓ ልጅና አባት የሚያሰኘው ዋናው ጉዳይም ይህ ነው፡፡ የክርስቲያኖች የንስሓ አባት የመያዛቸው መሠረታዊ ዓላማም ይህ ነው፡፡

መናዘዝ የሚለውን ቃል ስናነሣ በሉቃስ ወንጌል የተጻፈውን የጠፋውን ልጅ ታሪክ ማስታወስ ይገባል፡፡ አንድ አባት ሁለት ልጆች ነበሩት፡፡ ከሁለቱ ልጆች መካከል ታናሹ ከአባቱ ንብረት የሚደርሰውን ተካፍሎ ለመውጣት ፈለገ፡፡ አባቱም ከሀብቱ ለልጁ ሊደርሰው ይገባል ያለውን ድርሻውን ከፍሎ ሰጠው፡፡ ልጁም ድርሻውን ተቀብሎ ወደ ሩቅ ሀገር በመሔድ ሀብቱን አባክኖ ጨረሰው፡፡ ኋላም በሚኖርበት ሀገር ጽኑ ራብ በሆነ ጊዜ ለአንድ ገበሬ የእሪያ ጠባቂ ሆኖ ተቀጠረ፡፡ ረሃብ ስለጸናበትም እሪያዎች ከሚበሉት አሰር ሊመገብ ቢፈልግም የሚሰጠው አልነበረም፡፡ ረሃብ ሲጸናበት "ወደ ልቡ ተመልሶ እንዲህ አለ፦ እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በረሃብ እጠፋለሁ፡፡ ተነሥቼም ወደ አባቴ ልሔድ፡፡ አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ" አለ፡፡ ወደ አባቱ ሲሔድ አባቱ ገና ሩቅ ሳለ አይቶ አዘነለት፡፡ ሮጦም አንገቱን አቀፈና ሳመው፡፡ ጎረቤቶቹንም ጠርቶ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም፡፡ ደስም ይበለን ብሎ ታላቅ ድግስ ደገሰ ይለናል (ሉቃ.፲፭፥ ፲፩-፴፪)፡፡

> **የተነሳሒ ድርሻ በፍጹም ልብ ከመመለስ በተጨማሪ የበደለውን መካስ፣ የቀማውን መመለስ እንዲሁም በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በዕንባና በዋይታ ወደ እግዚአብሔር ማልቀስ ነው፡፡ ይቅርታ ማድረግ ግን ምሕረትና ቸርነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነው የእግዚአብሔር ነው፡፡**

ይህን አምላካዊ ቃል  በቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ መሠረት ሊቃውንት በብዙ መንገድ ያመሠጥሩታል፡፡ እኛ ግን አንዱን ብቻ ብንመለከት የሁለት ልጆች አባት የተባለው የሁሉ ፈጣሪና አባት እግዚአብሔር ነው፡፡ ሁለቱ ልጆች ደግሞ ቅዱሳን መላእክትና አዳም /የሰው ልጆች/ ፣ የጠፋው ታናሹ ልጅ የተባለውም አዳም ፣ ወደ ልቡ መመለሱ ደግሞ ንስሓ ለመግባት መወሰኑን፣ ጥፋተኛ ነኝና ልጅህ ልሆን አይገባኝም አገልጋይህ አድርገኝ ማለቱም ጥፋተኛነቱን አምኖ፣ ተጸጽቶ መናዘዙን ያስረዳልናል፡፡

የሰው ልጅ የለበሰው ሥጋ ለኃጢአት የሚስማማ ከመሆኑ የተነሣ ዕለት ዕለት አውቆ በድፍረት፣ ሳያውቅ በስሕተት እንዲሁም በቸልተኝነት ሕገ እግዚአብሔርን ይተላለፋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከቤተ እግዚአብሔርና ከመንፈሳዊ አገልግሎት ይርቃል፡፡ ይህም የሕሊና ዕረፍት፣ የአእምሮ ሰላም፣ የልብ ደስታ እንዲሁም ሰማያዊ ርስትን የሚያወርስ ተስፋንም ያሳጣዋል፡፡ ያን ጊዜም ያዝናል፤ ይከፋል፤ ወደ ልቡም ተመልሶ መፍትሔ  ይፈልጋል፡፡ መፍትሔውም ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ ሽማግሌ መፈለግ ነው፡፡ ይህ ሽማግሌም ካህን ነው፡፡ ካህኑም እንደ ሽማግሌነቱ ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቀኝ ብሎ የመጣበትን ሰው አስታርቅህ ዘንድ ጥፋትህ ምንድን ነው ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ እርቅ ፈላጊውም ጥፋቱን (ኃጢአቱን) ዘርዝሮ ይናገራል፡፡ መናዘዝ የሚባለውም ይህ ነው፡፡

ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ ሥርዓት በኦሪት የነበረ፣ በወንጌል የቀጠለ ነው፡፡ ለምሳሌ በኦሪት “ወንድ ወይም ሴት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይተላለፍ ዘንድ ሰው የሚሠራውን ኃጢአት ቢሠራ በዚያም ሰው ላይ በደል ቢሆንበት በሠራው ኃጢአቱ ላይ ይናዘዝ” (ዘፀ.፭፥፯) ተብሎ ተጽፏል፡፡  ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ እንደሚገባ ለምጻሞች ቀርበው ኢየሱስ ሆይ ማረን እያሉ ወደ እርሱ ሲመጡ “ወደ ካህን ሒዱና ራሳችሁን አስመርምሩ” በማለት ወደ ካህናት ልኳቸዋል፡፡ ሔደውም ራሳቸውን ለካህን ሲያስመረምሩ (ኃጢአታቸውን ሲናዘዙ) ከበደላቸው ነጽተዋል(ሉቃ.፲፯፥፲፪-፲፭)፡፡ ራስህን ለካህን አሳይ ያለውም ለምጽ በኃጢአት ምክንያት የሚመጣ በሽታ ስለነበረ (ዘሌ.፲፫፥፵፭-፵፯) ከጊዜያዊውም፣ ለዳግም ሞት ከሚያበቃው ሞትም እንዲድን ነው፡፡  ለኃጢአት በሽታ መድኃኒቱ ንስሓ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡

## ፪. ቀኖናን ተቀብሎ መፈጸም

ቀኖና (canon) የሚለው ቃል ምንጩ ጽርዕ (የግሪክ) ነው፡፡ ትርጓሜውም መቃ፣ መስፈሪያ፣ መለኪያ፣ መለካት መቍጠር ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ፲፱፻፵፰፣ ገ.፯፻፺፱)፡፡ ከንስሓ ጋር በተያያዘ ያለው ትርጉም “አንድ ተነሳሒ በካህኑ ፊት ኃጢአቱን ከተናዘዘ በኋላ ካህኑ ለኃጢአት ማስተሥረያ የሚሰጠው የመንፈሳዊ ቅጣት መጠንና ዓይነት” ማለት ነው፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ሁሉ ካህኑ ኃጢአተኛውን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ ሽማግሌ እንደ መሆኑ መጠን እርቁ እንዲፈጸም ጥፋተኛው ግለሰብ የሚጠበቅበትን መንፈሳዊ ግዴታ ለይቶ ማሳወቁ የማይቀር ነው፡፡ ምክንያቱም እርቅ ሲደረግ የበደለው አካል ይቅርታ ለማግኘት፣ የተበደለው አካል ደግሞ ይቅርታ ለማድረግ በየግላቸው ሊወጡት የሚገባቸው ድርሻ አለና፡፡ በዚህም መሠረት የተነሳሒ ድርሻ በፍጹም ልብ ከመመለስ በተጨማሪ የበደለውን መካስ፣ የቀማውን መመለስ እንዲሁም በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በዕንባና በዋይታ ወደ እግዚአብሔር ማልቀስ ነው፡፡ ይቅርታ ማድረግ ግን ምሕረትና ቸርነት የባሕርይ ገንዘቡ  የሆነው የእግዚአብሔር ነው፡፡

ካህኑ ለኃጢአተኛው ሰው እግዚአብሔር ይቅር ይልህ ዘንድ መንፈሳዊ ተግባራትን ፈጽም ብሎ የሚያዝዘው ትእዛዝ ቀኖና ይባላል፡፡ ይኸውም በብሉይ ኪዳን የኃጢአት፣ የበደል፣ የደኅንነት ወዘተ. መሥዋዕት ተብለው የፍየል፣ የበግ፣ የርግብ ወዘተ መሥዋዕት በማቅረብ ይፈጸም የነበረ ሲሆን በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ጹም፣ ጸልይ፣ ስገድ፣ መጽውት የሚለው መጠን እንደካህኑ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ቀኖና በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አስተምህሮ መሠረት ሰው ከስሕተቱ የሚታረምበት መንፈሳዊ ተግሣጽ ሲሆን ይህ ግን ምድራውያን ነገሥታት ለወንጀለኞች እንደሚሰጡት ቅጣት የሚታይ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ይቅር የሚለው ኃጢአተኛነቱን አምኖ በማዘኑ፣ በመቆጨቱና ከጥፋቱ በመመለሱ እንጂ ስለበደሉ በሚከፍለው ካሳ ብዛት አይደለምና፡፡ ለዚህም ቀደም ብለን ባየነው የጠፋው ልጅ ታሪክ ላይ ልጁ ለመናዘዝ ወደ አባቱ እየመጣ ሳለ “አባቱ ግን ገና ሩቅ ሳለ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው” (ሉቃ.፲፭፥፳) የሚለው የሚያሳየው የአባቱን ርኅራኄ እንጂ ቀኖናው ከኃጢአቱ አቻ መሆኑን አይደለም፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ “የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና” (፩ኛ ጴጥ.፬፥፫) ባለው መሠረት ነው፡፡አባቶቻችንም ይህንን መሠረታዊ ትምህርት አብነት አድርገው ኃጢአተኛው በኃጢአት ባሳለፈበት ዘመን ፈንታ ቀሪ ዘመኑን በጽድቅ ጎዳና እንዲመላለስ የሚያበቃውን ቀኖና ይሰጡታል፡፡ ሐዋርያው “የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና”  በማለት መናገሩ ከተመለሳችሁ ይበቃል ማለቱ አይደለም፡፡ በኃጢአት ፈንታ ፈቃደ እግዚአብሔርን ፈጽሙ ማለቱ እንጂ፡፡ አባቶች ካህናትም በዚሁ መሠረት ለኃጢአተኛ ሰው በቀማህበት ፈንታ መጽውት፣ ያለ ልክ በመብላትና በመጠጣት፣ በስካር፣ በኃጢአት ባሳለፍክበት ዘመን ፈንታ ጹም፣ ጸልይ፣ ስገድ በማለት ለኃጢአተኛው ቀኖና የሚሰጡት መንፈሳዊውን ጣዕም እንዲቀምስ ነው፡፡

እንዲያውም አባቶቻችን ለባለጸጋ ጾምን፣ ምንም ለሌለው ድሃ ምጽዋትን በማዘዝ ኃጢአተኞች ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመፈጸም በሰውነታቸው ላይ ጨክነው መወሰንን እንዲለማመዱ ያዛሉ፡፡ ምክንያቱም ለባለጸጋ ምግብ በቤት ውስጥ ሞልቶ ተርፎ እያለ መጾም፣ ለድሃ ደግሞ ቆጥቦ ያስቀመጠውን ወይም ለምኖ ያገኘውን ገንዘብ መመጽወት ከባድ ነውና፡፡ ይሁንና ድሃ ጦሙን አድሮም ቢሆን ይመጸውታል፤ ባለጸጋም ለተወሰነ ቀን ነውና እንደምንም ራቡን ታግሦ ይጾማል፡፡ ከዚህም

የተነሣ ሰውነታቸው ኃጢአትን ከመጸየፍ በተጨማሪ ለጽድቅ መታዘዝንም ይለማመዳል፡፡ ስለዚህ ተነሳሕያን የሚሰጣቸውን ቀኖና በዛ ብለው ሳያንጎራጉሩ፣ አነሰም ብለው ሳይጠራጠሩ በካህኑ ቀኖና ላይ የእግዚአብሔር ቸርነት እና የተነሳሒው ትሩፋት ተጨምሮበት ከታላቅ በደልና ኃጢአት እንደሚያነፃቸው አምነው ቀኖናቸውን ተቀብለው መፈጸም ይገባቸዋል፡፡

## ፫. ሥጋውንና ደሙን መቀበል

በክርስትና አስተምህሮ የአገልግሎቶች ሁሉ መደምደሚያው ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል ነው፡፡ የካህናትና የመምህራን መሾም ዋና ግቡ ምእመናንን አስተምረው ለሥጋውና ለደሙ ማብቃት ነው፡፡ ምክንያቱም የመንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ ግቡ ሰማያዊ ርስት መውረስ ነውና፡፡ ያለክርስቶስ ሥጋና ደም ደግሞ ሰማያዊ ርስት ማለትም የዘለዓለም ሕይወት የለም፡፡ ምክንያቱም "..እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፤ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም" (ዮሐ.፮፣ ፶) ተብሎ ተጽፏልና፡፡

በጠፋው ልጅ ታሪክ አስቀድመን እንደተመለከትነው ልጁ ወደ አባቱ ቤት ሲመለስ አባቱ ፍሪዳ አርዶ፣ ድግስ ደግሶ ተቀብሎታል፡፡ የጠፋው ልጅ አዳም ነው፡፡ የጠፋውን አዳምን ፍለጋ የመጣው ደግሞ ክርስቶስ ነው፡፡ "የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና" (ሉቃ.፲፱፥፲) እንዲል፡፡ ለአዳም ልጆች የሕይወት ምግብ ሊሆን የታረደው ፍሪዳም ራሱ ክርስቶስ ነው፡፡ በቀራንዮ ኮረብታ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ፣ ደሙን አፍስሶ መሥዋዕት ሆኗልና፡፡ ጌታችን በዕለተ ዓርብ መሥዋዕት ከመሆኑ አስቀድሞ ሐሙስ ማታ "እንጀራን አንሥቶ ባርኮ ቈርሶ እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው፤ እንዲሁም ጽዋውን አንሥቶ አመስግኖ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴ.፳፮፥፳፮) በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህም የክርስቶስ ሥጋና ደም ለእኛ የሕይወት ምግብና መጠጥ ሆኖ መቅረቡን የሚናገር ነው፡፡

ስለዚህ እኛም የዘለዓለም ሕይወት ለማግኘትና ሰማያዊ ርስትን ለመውረስ የክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበል ይኖርብናል፡፡ "ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡ ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል" (ዮሐ.፮፥፶፮-፶፯) የሚለውም ይህንኑ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በኦሪቱ በነበረው የመሥዋዕት ሕግ እስራኤላውያን የፋሲካውን በግ ሲመገቡ ጫማቸውን ተጫምተው፣ ወገባቸውን ታጥቀው፣ ኩፌታቸውን ደፍተው በትራቸውን ይዘው እየተቻኮሉ እንዲመገቡ ታዘው ነበር (ዘፀ.፲፪፥፲፩)፡፡ ይህም ዛሬ ላለነው ክርስቲያኖች ምሳሌ ሆኖን የአማናዊውን በግ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን ስንቀበል በጎ ምግባር ሠርተን፣ ወንጌሉን ተጫምተን፣ የንጽሕናን ዝናር ታጥቀን፣ አክሊለ ሦክን፣ ነገረ መስቀሉን እየዘከርን (መስቀሉን ተመርኩዘን)፣ ሞት እንዳለብን በማሰብ እንዳይቀድመን ፈጥነን ንስሓ በመግባት ሥጋውንና ደሙን መመገብ የሚገባን መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

ቀደም ብለን ባየነው የጠፋው ልጅ ታሪክም አባት ልጁ ከጠፋበት ሲመለስ ፊሪዳውን ከማረዱ በፊት "ባሪያዎቹን ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት፣ ለእግሩም ጫማ ስጡት" በማለት ልጁ ታጥቦ ንጹሕ የሆነውን ልብስ ለብሶና አዲስ ጫማ ተጫምቶ እንዲዘጋጅ ነበር ያደረገው፡፡ ልጁን ወደ ልቡ እንዲመለስና የአባቱን ቤት እንዲያስብ ያደረገው ረሃብ ነበር፡፡ "እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ አለ" በማለት መናገሩ ምስክር ነው፡፡ ከአባቱ ቤት ካለው ማዕድ ለመቀበል ግን አስቀድሞ ያንን ማዕድ አቋርጦ በመውጣት የበደለውን አባቱን ይቅርታ መጠየቅ ነበረበት፡፡

ስለሆነም አባቱን ማረኝ አለው፡፡ አባቱም ይቅር አለው፡፡ ከዚያ በኋላ ከፊሪዳው ተመገበ፡፡ እኛም ገና በአርባና በሰማንያ ቀናችን ጀምረን ስንመገብ የኖርነውን ሥጋውንና ደሙን መቀበል አቋርጠን ወደ ተለያየ የኃጢአት ሕይወት ብንገባም እንኳ ወደ ልባችን ተመልሰን ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል ስንመጣ አስቀድመን ስለጥፋታችን ይቅርታ መጠየቅ እንደሚገባን ያስገነዝበናል፡፡ ይህም ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል ንስሐ ገብተን መዘጋጀት የሚገባ መሆኑን ይገልጣል፡፡ አንድም የንስሓ ጉዞ መጨረሻው በክርስቶስ ሥጋና ደም መታተም የሚገባው መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡

በአጠቃላይ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ከተለየ በንስሓ መመለስ ይኖርበታል፡፡ እግዚአብሔር አምላካችንም በነቢዩ ላይ አድሮ አምላካዊ ጥሪውን ያስተላለፈውና "ወደ እኔ ተመለሱ" እያለ የሚጠራን ለንስሓ ነው፡፡ ስለሆነም ሁላችንም በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን፣ ቅዱስ ሥጋውን በልተን፣ ክቡር ደሙን ጠጥተን ከቅዱሳን ማኅበር እንዲጨምረን የሚጠበቅብንን መወጣት አለብን፡፡ በንስሓ ተመልሰን በቤቱ እንድንኖር እግዚአብሔር በቸርነቱ፣ ቅዱሳን በአማላጅነታቸው አይለዩን፡፡ አሜን!! ☩

# ተስፋ አያሳፍርም

**(ሮሜ ፭፥፭)**

ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን

የሰው ልጅ ጥንት አታድርግ የተባለውን ሲያደርግ፣ አትብላ የተባለውን ሲበላ የተሰጠውን ተነጠቀ፤ ልጅነቱን፣ ገዥነቱን፣ ክብሩን ወዘተ. አጣ። ይሁን እንጂ በተሰጠው አእምሮ ተጠቅሞ በሠራው ስሕተት ተጸጸተ፤ የበደለውን አምላኩን ይቅር በለኝ በማለት አነባ። የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሣ አምላክ ጽኑዕ የሆነ ቃል ኪዳን ሰጠውና የተወሰደችበትን ልጅነት በዚህም ምክንያት ያጣትን ርስት፣ እንደሚያገኝ ጸኑዕ ተስፋን ሰንቆ በተፈቀደለት ምድር መኖር ጀመረ። ዛሬም ቢሆን ሰው አእምሮውን ጨርሶ ካላጣ በቀር ባለተስፋ ነው። ምን አልባት ተስፋ የሚያደርገው ነገር ይለያይ እንደሆነ እንጂ በውስጡ ተስፋውን ሰንቆ የማይጓዝ የለም።

አንዳንዱ ሥራውን ተስፋ ያደርጋል፤ አንዳንዱ ትምህርቱን ተስፋ ያደርጋል፤ አንዳንዱ ሀብቱን ተስፋ ያደርጋል። ይህ ሁሉ ግን የሚያዋጣ አይደለም። ምክንያቱም አንድ ቀን ያልፋልና፤ ጭንቅ ሲመጣ ከመጣው መከራ አያድንም ራሱም አይድንም። ክርስትናውን በአግባቡ የተረዳው ደግሞ ፈጣሪውን ተስፋ ያደርጋል። ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ "ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው።" (ሰቆ. ኤር. ፫፥፳፮) እንዲል። ስለዚህ ሰዎች እግዚአብሔር አምላካቸውን በማመን ማዳኑን ፣ ጥበቃውን፣ መግቦቱን፣ ይልቁንም ለሰው ልጅ ያለውን ጽኑዕ ፍቅር በማሰብ ተስፋ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በዚህ ጽሑፉ የተስፋን ምንነት፣ ተስፋ የሚያስቆርጡ ፣ በተስፋ ብንኖር የምናገኛቸውን ነገሮችና መሰል ጉዳዮችን እንመለከታለን።

## ተስፋ ምንድን ነው?

ተስፋ ወደፊት እንዲሆንልን፣ እንዲደረግልን፣ እንዲሰጠን የምንፈልገውን ነገር ይሆንልኛል፤ ይሰጠኛል፤ ይደረግልኛል ብሎ ማመን ነው። ይህንንም አስመልክተው ደስታ ተክለ ወልድ ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በተሰኘ መጽሐፋቸው "ተስፋ፡- አለኝታ፣ ወደፊት አገኛለሁ የማለት ጽኑዕ እምነት" (ገጽ ፲፪፻፸፬) በማለት ይገልጹታል። ስለሆነም እንደ እርሳቸው አገላለጽ ተስፋ ማለት የወደፊት ምኞት፣ አገኛለሁ፣ ይሆንልኛል፣ ይደረግልኛል የሚል ጽኑዕ እምነት እንደሆነ ነው።

ተስፋ በክርስትና ሕይወት መሠረታዊው ጉዳይ ነው። ሰው በሚያየውና በሚጨብጠው ነገር ቢተማመን ምንም የሚያስደንቅ ነገር የለውም። ነገር ግን በሥጋዊ ዐይን የማያዩትን፣ በሥጋዊ እጅ የማይዳስሱትንና የማይጨብጡትን አምላክ "የፈለግሁትን ይሰጠኛል፤ የሚጠቅመኝን ያደርግልኛል ለምኘው አያሳፍረኝም" ብሎ ማመን እጅግ የሚደንቅ ነገር ነው። ስለሆነም በሃይማኖት ስንኖር ዋናው እና ትልቁ መሣሪያችን ተስፋ ነው። ሃይማኖት ፈጣሬ ሰማያት ወምድር የሆነውን እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ ነው የተባለውም ለዚህም ነው።

ተስፋ የሚታየውን በማይታየው ይቀይራል። አብርሃም በሽምግልና ዘመኑ ያገኘውን አንድ ልጁን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው በዐይነ ሥጋ ሳይሆን በዐይነ ሕሊና የሚታይ የተሻለ ጥቅም ስለነበረው ነው። በመጽሐፍ "አብርሃምም እግዚአብሔር በፈተነው ጊዜ ልጁን ይስሐቅን ይሠዋው ዘንድ በእምነት ወሰደው። በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል ብሎ ተስፋ ያደረገለትን አንድ ልጁን አቀረበው። እግዚአብሔር ከሙታን ለይቶ ሊያስነሣው እንደሚችል አምኗልና፤ ስለዚህም ያው የተሰጠው መታሰቢያ ሆነለት (ዕብ.፲፩፥፲፯-፲፱፤ ዘፍ.፲፪፥፩) ተብሎ የተነገረው ለዚህ ነው። አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ በተስፋም ከሚያውቀው ሀገር፣ ከሚያውቀው ሕዝብ ወጥቶ ወደማያውቀው ሀገር፣ ወደማያውቀው ሕዝብ ሔደ።

በሰው ሰውኛው ሲታይ አብርሃም የፈጸመው ትክክል አይደለም ሊባል ይችላል። ምክንያቱም "በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል" እየተባለ ያንኑ የዘሩ መጠሪያ የሆነውን ሠዋ ሲባል 'እሺ' ብሎ መሔድ ምን ያህል እምነትና ጽኑዕ ተስፋ እንዳለው የሚያስረዳ ነው። አብርሃም አንድ ልጁን ለእግዚአብሔር አልከለከለውም፤ እንዲሁ እግዚአብሔርም አንድያ ልጁን ለአብርሃም አልከለከለውም። እንኳን ለአብርሃም በእምነት ለታዘዘው፣ የሚታየውን በማይታየው ለውጦ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጎ ከሀገሩ ለወጣው ይቅርና ለጠላቶቹ እንኳን አልከለከላቸውም። የእግዚአብሔርን ቃል መስማት በእንደዚህ ያለ ጽኑዕ ተስፋ ያኖራል፤ በተስፋ መኖር ብቻም ሳይሆን ከክፉ ሁሉ ያለ ድንጋጤ ያሳርፋል። ስለሆነም "ተስፋ አያሳፍርም" በማለት ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የገለጸውን ልብ ማለትና በልቡና ሠሌዳ ማተም ያስፈልጋል።

ተስፋ በምቾት ጊዜ፣ ምንም መከራና ፈተና በሌለበት ወቅት ሳይሆን በሰው ሰውኛው አይቻልም በሚባልበት የጭንቅና የመከራ ዘመን ሊታጠቁት የሚገባ ረቂቅ መሣሪያ ነው።

## ተስፋ መቁረጥ ከምን ሊመጣ ይችላል?

ሰዎች ሥጋዊ ፍላጎት በሚያይልበት ዓለም፣ የክፋት፣ የተንኮል፣ የኃጢአት ወሬ በሚሰማበት ዓለም እየኖሩ የዚህ ችግር ሰለባ ሳይሆኑ በሃይማኖት ጸንተው በጎ ምግባር ሠርተው መኖር ባለመቻላቸው ተስፋ ይቆርጣሉ። ተስፋ የሚቆርጡባቸው ምክንያቶች ደግሞ በርካታ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ክፍል ግን የተወሱትን ብቻ እንመለከታለን።

## ፩. የእግዚአብሔርን ቃል አለመስማት

እግዚአብሔር አስቀድሞ መስማት እንድንችል ጆሮ፣ እንድናስተውል አእምሮ፣ የሰማነውን ደግሞ በተግባር ማዋል የሚያስችል አቅም ፈጥሮልናል። መቼም ቢሆን እኛ የማንችለውን አላዘዘንም፤ አያዝንምም። ነገር ግን የምንችለውን ባለማድረጋችን ሁል ጊዜም ስንጎዳ እንኖራለን። አዳም የእግዚአብሔርን ቃል ባለመስማት ተጎዳ፤ በርካታ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ባለመስማት ተጎዱ፣ ሰብአ ትካትን፣ ሰብአ ሰዶምን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። በአንጻሩ የእግዚአብሔርን ቃል የሰሙት የነነዌ ሰዎች ደግሞ ከመጣባቸው መዓት ድነዋል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ማለት አድርጉ የተባልነውን ማድረግ፣ አታድርጉ የተባልነውን ደግሞ አለማድረግ ነው፤ ቃሉ ሕይወት ነውና። ወንጌላዊው ዮሐንስ በመልእክቱ "ንዜንወክሙ በእንተ ውእቱ ዘሀሎ እምቅድም ውእቱ ዘሰማዕናሁ በዕዘኒነ ወዘርኢናሁ በአዕይንቲነ ወዘጠየቅናሁ ወዘገሠሣሁ እደዊነ በእንተ ነገረ ሕይወት፤ ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረውንና በጆሯችን የሰማነውን በዓይናችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን" በማለት ስሙት የተባልነው ቃል የሕይወት ቃል እንደሆነ ጽፎልናል። (፩ዮሐ.፩፥፩)

መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን "ቃሌን የሚሰማ ግን በተስፋ ይኖራል፤ ከክፉም ሁሉ ያለድንጋጤ ያርፋል" (ምሳ. ፩፥፴፫) በማለት የገለጸውን ማስታወስ ያስፈልጋል። የእስራኤል ንጉሥ ጠቢቡ ሰሎሞን በንግሥናው ዘመን ለሕዝቡ በምሳሌ ቃሌን ስሙ እያለ በተደጋጋሚ ይናገር ነበር። ነገር ግን ቃሌን ስሙ የሚለው የእርሱን ቃል ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ደግሞ ጥበበኛ ያደርጋል፤ ተስፋን ያለመልማል፤ ከክፉም ይታደጋል። ስለዚህ "ቃሌን የሚሰማ ግን በተስፋ ይኖራል፤ ከክፉም ሁሉ ያለድንጋጤ ያርፋል" በማለት ያስረዳናል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ በተስፋ ይኖራል በአንጻሩ የእግዚአብሔርን ቃል የማይሰማ ግን ተስፋ ይቆርጣል።

## ፪. በሐሰተኛ ትምህርት መሞላት

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ምእመናን በላከው መልእክቱ "ሌላ ልዩ ትምህርት አታምጡ፤ ልባችሁ በመብል ያይደለ በጸጋ ቢጸና ይበልጣልና፤ በዚያ ይሔዱ የነበሩት እነዚያ አልተጠቀሙምና" (ዕብ. ፲፫፥፱) በማለት እንደገለጸው ለምእመናን የማይገባ ትምህርት ተስፋ ያስቆርጣል።

በዘመናችን እየተስተዋለ ያለው የወጣቱ የሥነ ምግባር ዝቅጠት መማር ያለበትን ሳይሆን መማር የሌለበትን የሐሰት ትምህርት እየተማረ ስላደገ ነው። በእናት በአባቶቹ ተስፋ የቆረጠ፣ በሀገሩ ተስፋ የቆረጠ፣ ለማንነቱ ዋጋ የማይሰጥ፣ ከሰውነት የወጣ ሥራ እየሠራ ያለው፣ የተማረው ትምህርት የሚገነባ ሳይሆን የሚያፈርስ፣ ተስፋ የሚያስሰንቅ ሳይሆን ተስፋ የሚያስቆርጥ ስለሆነ ነው።

## ፫. ለምድራዊ ሕይወት መጨነቅ

የሰው ልጅ ፍላጎቱ የበዛ በውስጡ ያለውን ፍላጎት ለማሟላት ያለው አቅም ግን እጅግ ውሱን የሆነ ፍጥረት ነው። ፍላጎቱ ከመብዛቱ የተነሣ በሚጠቅመውም በማይጠቅመውም፣ በሚያስፈልገውም በማያስፈልገውም፣ በሚያስደስተውም በማያስድስተውም ብቻ በብዙ ነገር ይጨነቃል።

ይልቁንም በዘመናችን እንደተከሠተው ዓይነት ለዓለም ስጋት የሆነ፣ በሰው ሰውኛ ሠልጥነናል ያሉ ሀገራት ሊቋቋሙት ያልቻሉት በሽታ፣ በሃይማኖታቸውና በዘራቸው እየተለዩ እንደ በግ የሚታረዱበት ሁኔታ ሲከሠት ሰዎች እጅግ ይጨነቃሉ። ይሁን እንጂ አለማሰብ ባይቻልም አለመጨነቅ ግን ይቻላል። ይቻላል ብቻ ሳይሆን እንዳንጨነቅም ታዝዛናል። መድኀኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ እንዳንጨነቅ ብቻ ሳይሆን በመጨነቃችን አንዳች የምንጨምረው ነገር እንደሌለን "ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማነው" (ማቴ. ፮፥፳፯) በማለት አስተምሮናል።

ስለሆነም ምእመናን ከአላስፈላጊ ጭንቀት ወጥተው እንዲያደርጉ የታዘዙትንና ማድረግም የሚችሉትን ብቻ እያደረጉ በሌላው ነገር ሁሉ ግን እግዚአብሔርን በመለመን እርሱን ብቻ ተስፋ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ሰዓት የመምህራን ድርሻም የሚሆነው የተባለውንም ሆነ ያልተባለውን ምእመናን የሚያንጸውንም ሆነ የሚያፈርሰውን እየተናገሩ በጭንቀት ላይ ጭንቀት ከመደራረብ ተቆጥበው የሚያጸናውንና የሚያጽናናውን የእግዚአብሔርን ቃል ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ምእመናን መማር የሚገባቸውን መሠረታዊ ትምህርት ባይማሩ ከላይ እንደተገለጸው በሐሰተኛ ትምህርት ተሞልተው፣ ለምድራዊው ሕይወት ብቻ እየተጨነቁ ተስፋ መቁረጥ ላይ ሊደርሱ ይችላሉና መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

## ፬. የመከራ ጽናት

ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን በየጊዜው ልዩ ልዩ መከራ ሲፈራረቅባቸው ኖረዋል። በዘመናችንም እጅግ የሚከብድና የሚዘገንን መከራ እየደረሰብን ነው። በዚህ ዓለም እስከ ኖሩና የክርስቶስንና የክርስቶስ ወዳጆች የሆኑትን ቅዱሳን አብነት እስካደረጉ ድረስ ወደ ፊትም መከራው ሊቀጥል ይችላል። ከ፳፻፲፩ ዓ.ም ጀምሮ በሁለት በሦስት ዓመታት ውስጥ ካሳለፍናቸው ዐሥር ዐሥራ አምስት ዓመታት በተለየ መልኩ መከራው የተፈራረቀባቸው ዓመታት ነበሩ። መከራው ሰው ሠራሽም ተፈጥሯዊም፣ መንግሥታዊም፣ ግለሰባዊም፣ የውስጥም የውጭም ሊባል ይችላል። ተፈጥሯዊ ሲባል የጎርፍና የእሳት አደጋዎች፣ በድርቅ ምክንያት የሚከሠት ጽኑዕ ረኀብና ዓለማቀፋዊውን መቅሰፍት የኮቪድ ፲፱ ወረርሽኝን ጨምሮ መጥቀስ ይቻላል። ሰው ሠራሽ ደግሞ የእርስ በእርስ ጦርነት፣ የዘር ጭፍጨፋ፣ የአብያተ ክርስቲያናት መቃጠል፣ የሰዎች ከቀያቸው መፈናቀል፣ ወዘተ. ሁሉ ተጠቃሽ ናቸው።

መከራው የሰው ልጅ መከላከል የሚችለውም የማይችለውም ነው፡፡ ተፈጥሯዊ የሆነውን መከላከል ባይችልም ሰው ሠራሹን ግን መከላከል ይቻል ነበር፡፡ ይህ ማለት በቀጥታ አደጋው የደረሰበት አካል መከላከል ባይችልም አደጋውን ያመጣው አካል እንዲሁም የሚመለከተው የመንግሥት አካል መከላከል ይችል ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ በሚከብድና በሚዘገንን መከራም ቢሆን ከ፲፱፻፲፫ ዓ.ም ወደ ፳፻፲፬ ዓ.ም ተሸጋግረናል፡፡ በመሆኑም ሰዎች የዚህ ከባድ መከራ ተሸካሚ ሲሆኑ የጸኑት መከራውን ተቋቁመው ሊያልፉ ይችላሉ፡፡ ያልጸኑት ደግሞ ተስፋ ቆርጠው ሃይማኖታቸውን እስከ መለወጥም ሊደርሱ ይችላሉና የመከራው ጽናት የተስፋ መቁረጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

## በተስፋ መኖር የሚያስገኘው ጥቅም

### ፩. ከክፉ ያሳርፋል

የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና በተስፋ መኖር ከክፉ እንድንድን ያደርጋል፡፡ በሐዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ጽኑዕ የሆነውን ተስፋ የሰነቁት ሐዋርያት እሳቱን እና ስለቱን ታግሠው ለበለጠ ክብር በቅተዋል፡፡ ከመካከላቸው የእግዚአብሔርን ቃል ያልሰማው ይሁዳ ግን ተለይቷል፤ አልሰማም ማለት በዕዝነ ሥጋው አልሰማም ማለት አይደለም፤ በዕዝነ ልቡናው ግን በእርግጥም አልሰማም፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን ከሐዋርያት ጋር ቢቆጠርም፣ ትምህርቱ፣ ተአምራቱ ባይነፈገውም ክብርን ግን አላገኘም፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በአግባቡ አልሰማምና፡፡ (ኢሳ.፯፥፩-፲)

ምን አልባትም በተስፋ ከመኖር ይልቅ ተስፋ በመቁረጡ ግኡዝ የሆነችው እንጨት ብትመክረው እንኳን መመለስ አልቻለም፡፡ በተስፋ መኖር እንደፈያታዊ ዘየማን የመጨረሻ ሕይወትን ያሳምራል፡፡ ተስፋ መቁረጥ ግን እንደይሁዳ በመጨረሻ ከቤት መውጣትን እስከ መጨረሻው አለመመለስን ያስከትላል፡፡ ተስፋ መቁረጥ እጅግ የከፋ አደጋ ላይ ይጥላልና፡፡

በዘመናችንም ሰው የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ስለማያደርግ ሥጋዊ መፍትሔ ብቻ ይታየዋል፡፡ በእርግጥ ሥጋዊ መፍትሔውም የሚገኘው በእግዚአብሔር ነው፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሥጋም የነፍስም መድኃኒት እንደሆነ አለመቀበል በብዙኃኑ ዘንድ ይስተዋላል፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ካለማድረግ የመጣ ነው፡፡ ሥጋዊ ዕውቀትን ብቻ ተምሮ ያደገ ሰው ሁሌም የሚታየው ሥጋዊ ድሎት ነው፤ "በቃልህ እዘዝ፤ ልጄ ይድናል" ያለው የመቶ አለቃው ቃል ትዝም አይለው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ባለመስማቱም በመጨነቅ፣ በመሸበር፣ ለውጥ የማያመጣ መፍትሔ ሲያፈላልግ ዘመኑን በከንቱ ይጨርሳል፡፡ (ማቴ. ፰፥፰)

የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ማድረግና በጽኑዕ ተስፋ መኖር የተስፋ ቃሉንም በትክክል ሰምቶ በተግባር ላይ ማዋል ከክፉ የሚታደገን መሆኑን ሐዋርያው ያዕቆብ "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ፡፡ ቃሉን ሰምቶ የማያደርገው ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስታዎት እንደሚያይ ሰው ይመስላል፡፡ ራሱንም ተረድቶ ይሔዳል፤ ወዲያውም እንዴት እንደሆነ ይረሳል" (ያዕ.፩፥፳፪) በማለት ያስረዳናል፡፡ ይህ ማለት የተስፋ ቃሉን ሰምቶ በሕይወት መተርጎም ይገባል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሕይወት ነው፤ ከክፉም ያለምንም ድንጋጤ ያድናል፡፡

ያሳለፍነው ዘመን እጅግ የከፋ መከራው የተፈራረቀበት ዘመን እንደነበር ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ተስፋ አያሳፍርም" በማለት እንደነገረን የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ አድርገን መልካሙን ዘመን እንዲያመጣልን፣ የክፉዎችንም ልቡና እንዲያራራልን፣ የተፈጥሮውንም ሆነ ሰው ሠራሹን አደጋ በቸርነቱ እንዲያስታግሥልን አጥብቀን መለመን ይኖርብናል፡፡ እግዚአብሔር አምላካችን በጽኑዕ ተስፋ እንደሚያ ደርግልን አምነን በጸሎት እንጠይቀዋለን፤ እርሱም የጠየቅነውን ሁሉ ያደርግልናልና፡፡

### ፪. የመንግሥተ ሰማያት ወራሽ ያደርጋል፡፡

ሰው ከሞተ በኋላ በእግዚአብሔር ዘንድ በሕይወት እንደሚኖር ባለመጠራጠር ማመን ይገባል፡፡ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ምእመናን በላከው መልእክቱ "ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ እንደተነሣ ካመንን እንዲሁ እግዚአብሔር ሙታንን በኢየሱስ ያስነሣቸዋል፤ ከእርሱም ጋር ያመጣቸዋል" በማለት እንዳስረዳን በሥጋዊ ዐይናችን ሳናይ ሰምተን ብቻ የተቀበልነው ሃይማኖት ነው፡፡ (፩ኛ ተሰ. ፬፥፲፬) በዐይን የማይታየውን በእጅ የማይዳሰሰውን መውረስ ደግሞ በጽኑዕ ተስፋ የመኖር ውጤት ነው፡፡

> **የእግዚአብሔርን ቃል መስማት በእንደዚህ ያለ ጽኑዕ ተስፋ ያኖራል፤ በተስፋ መኖር ብቻም ሳይሆን ከክፉ ሁሉ ያለ ድንጋጤ ያሳርፋል፡፡ ስለሆነም "ተስፋ አያሳፍርም" በማለት ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የገለጸውን ልብ ማለትና በልቡና ሠሌዳ ማተም ያስፈልጋል፡፡**

መንግሥተ ሰማያት እንዳለች፣ እንደምንወርሳት፣ በደስታ እንደምንኖርባት ከአወቅን በኋላ እንደማናጣትም አምነን የተቀበልነው ለመንግሥተ ሰማያት የምታበቃውን ርትዕት የሆነችውን ሃይማኖት አጽንተን በእግዚአብሔርም ቸርነት እንወርሳታለን የሚለው ሙሉ ተስፋ ስላለን ነው።

ደግሞም ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ምእመናን በላከው መልእክቱ "እምነትስ ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የምታረጋግጥ፣ የማናየውንም ነገር የምታስረዳ ናት" ብሎ እንደነገረን ተስፋ የምናደርገው ነገር አለ፤ እርሱም መንግሥተ ሰማያት ነው። ይህን ተስፋ የምናደርገውን ነገር ደግሞ በእምነት እንወርሰዋለን። በሃይማኖት ጸንተን በጎ ምግባር ሠርተን ስንኖር ያን ተስፋ ያደረግነውን ርስት ሊያወርሰን እርሱ የታመነ አምላክ ነው። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው" በማለት ያስረዳናል። (ዕብ.፲፩፥፩፤ ፩ቆሮ.፩፥፱)

ቅዱስ ያሬድም በድርሰቱ "ተስፋ ሕይወት ተሠራ በሰማያት ተስፋ ሕይወት ተሠራ በሰማያት ተስፋ ሕይወት ተሠራ፤ የሕይወት ተስፋ በሰማያት ተሠራ" በማለት ሦስት ጊዜ እየደጋገመ ይነግረናል። ሊቁ በሰማያት ተሠራ ያለው የሕይወት ተስፋ በሃይማኖት ጸንተው በጎ ምግባር ሠርተው የሚወርሱት መንግሥተ ሰማያት ነው። የእግዚአብሔርን የባሕርይ አምላክነት፣ አምኖ፣ በዐይነ ሥጋ የማይታይ ዘለዓለማዊ መንግሥቱን ያወርሰኛል ብሎ በተስፋ ጸንቶ ለኖረ የሚወረስ ነውና እንዲህ በማለት ገለጸው።

ከጥንት ጀምሮ ቅዱሳን አበው እና ቅዱሳን ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት መከራ የተቀበሉት የማይቀር፣ የማያሳፍር ተስፋ ስለነበራቸው ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲገልጽ "እነርሱ በእምነት ተጋደሉ፤ ነገሥታትን ድል ነሡ፤ ጽድቅን አደረጉ፤ ተስፋቸውን አገኙ፤ የአናብስትን አፍ ዘጉ" (ዕብ.፲፩፥፴፫) ሲል ያስረዳል። እነርሱም የተጋደሉት በእምነት ነው፤ ተጋድለውም ነገሥታትን ድል አደረጉ፤ ይጠባበቁት የነበረውን ተስፋም አገኙ። ተስፋቸው ደግሞ ድኅነት ነው፤ ርስተ መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ነውና፤ ያመኑት ሆነላቸው።

በአጠቃላይ አባታችንን አዳምን ከገነት ሲያስወጣው ጽኑዕ ተስፋ ሰጥቶ በዚች ምድር እንዲኖር ያደረገ አምላክ የሰጠውንም ተስፋ ያላስቀረ ታማኝ አምላክ ዛሬም ከኖሩበት ቦታ ተፈናቅለው፣ በማንነታቸው ተሸማቅቀው፣ በአንድ በኩል በሰው ሠራሽ አደጋ በሌላ በኩል በተፈጥሮ አደጋ እየተጨነቁ ያሉት ሁሉ ተስፋ አያሳፍርምና በተስፋ እግዚአብሔርን መለመን ይኖርባቸዋል። ነቢየ እግዚአብሔር ዕንባቆም "በለስ አታፈራምና በወይኑም ፍሬ ሐረግ አይሆንም፤ ወይራ ሥራዋን አበለች እርሻዎችም እህልን አላፈሩም፤ በጎች ከግጦሽ ታጡ፤ ላሞችም በበረት ውስጥ አልተገኙም፤ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሤትን አደርጋለሁ። (ዕንባ. ፫፥፲፯-፲፰) በማለት እንደተናገረው በሃይማኖታችን ጸንተን በጎ ምግባር እየሠራን በእግዚአብሔር ቤት በተስፋ ልንኖር ይገባል።

በሚመጣብን መከራ ሁሉ በሃይማኖት ጸንተን፣ በጎ ምግባር ሠርተን፣ የተስፋውን ቃል በልቡናችን ማኅተም አትመን የምንችለውንና የሚጠበቅብንን ሁሉ ሠርተን በመጨረሻይቱ ዕለት "እናንተ የአባቴ ቡሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን የአባቴን መንግሥት ትወርሱ ዘንድ ወደ እኔ ኑ" የሚለውን የሕይወት ቃል ያሰማን ዘንድ እግዚአብሔር አምላካችን ይፍቀድልን አሜን። ✠

**መስቀል ዘአጥዕሞ ለማይ መሪር በገዳመ ሱር ሶበ ተወድየ ውስቴቱ በእደ ሙሴ፤ በሱር በርሃ የነበረው መራራ ውሃ በሙሴ እጅ መስቀል በተጨመረበት ጊዜ መራራው ውሃ ጣፈጠ"።**

ውዳሴ መስቀል ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

# ዘመኑ ለጽድቅ የምንበቃበትን ተግባር የምንፈጽምበት ይሁን

ዲ/ን አሻግሬ አምጤ

አምላካችን እግዚአብሔር አስጨናቂ መከራ የሚያመጣው ቢቀሰቅሰን አልነቃ ስንል ወይም በበረከት ሊጎበኝን ሲፈልግ ነው። ለነፍሳቸው ድኅነት የሚጨነቁ ብልሆች መከራ የመጣው እኔ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ እንድመለስ ነው ብለው ራሳቸውን ያዘጋጃሉ። በሌላ በኩል ደግሞ መከራ ሲመጣ ሳያልፍ የበለጠ ኃጢአት እንሥራ በማለት ዕለት ዕለት ኃጢአት የሚርባቸውና ለጥፋት የሚዘጋጁ ወገኖች አሉ። ከዚህ በተጨማሪም እግዚአብሔር እንዲህ ብለህ ተናገር ብሎ ልኮኛል ብለው የራሳቸውን ምኞት እየተናገሩ ራሳቸው በኃጢአት ተጨማልቀው ሕዝብ በኃጢአት ላይ ኃጢአት በመጨምር ከእግዚአብሔር እንዲለይ፣ በእግዚአብሔር ቊጣም እንዲጠፋ የሚገፋፉ አሉ። እንዲህ ብለው ሲናገሩ በቅቻለሁ እያሉን ስለሆነ ቃላቸው እውነት ሆኖ በተግባር ሲፈጸም ባየነው፣ መከራውም በራቀ ነበር።

ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው የተጨነቁት እንዲረጋጉ እንጂ ሰላማውያን የበለጠ እንዲሸበሩ አይደለም። ነቢዩ ኤርምያስ እግዚአብሔር ያዘዘውን ለቤተ አይሁድ በተናገረ ጊዜ የሐሰት ነቢያት የእግዚአብሔር ቃል እኛን ዐልፎ በየት በኩል ወደ አንተ መጣ ብለው በድፍረት እስከ መናገር ደርሰው ነበር። በዘመናችን የምናየውም በነቢዩ ዘመን የነበሩ አይሁድ ከፈጸሙት ቢከፋ እንጂ የተሻለ አይለይም። በዘመናችን ከእግዚአብሔር ቤት የሸፈቱ፣ አሁንም የመከራው መፈራረቅ ያላስተማራቸው ወገኖች ብዙ ናቸው። አገልጋዮች ነን የሚሉት እንኳን ሳይቀሩ ከቤተ መቅደሱ ሸፍተዋል፤ የጠቡትን ጡት የሚነክሱ፣ የበሉበትን ማዕድ የሚረግጡ ውለታ ቢሶች እየበዙ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን በጸሎት እንድንማጸነው ዓለምን የሚያስጨንቅ ጦርነት፣ ወረርሽኝ፣ የኃያላን ውረድ እንውረድ ይዋጣልን የሚሉ ዛቻዎች አስነሣ። መከራ ሲበዛ ጸጋ እግዚአብሔር መብዛቱን ሁል ጊዜ የምታስተምረው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንኳን ለልጆቿ ላሳዳጆቿ ስትጸልይ ኖራለች፤ ወደ ፊትም እስከ ምጽአት የምትጸልየው የሰው ልጅ ድኅነት ስለሚያሳስባት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ለሚያምነውም ለማያምነውም፣ ለሚገፋትም ለሚደግፋትም ስትጸልይ መኖሯን ለማረጋገጥ የፈለገ ሰው የምታደርገውን ቀርቦ ማየት ይችላል። ባሕርይዋን የማያውቁ ወገኖች በዘመናቸው የተነገረውን የጸሎት ዐዋጅ ሰምተው ቤተ ክርስቲያን ጸሎት መጸለይ የጀመረችው ዛሬ ይመስላቸዋል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ግን ስለ ሀገር ሰላም፣ ስለ ሕዝብ ደኅንነት ጸሎት ምህላ የጀመረችው በዓለመ መላእክት ከነበረችበት ጊዜ አንሥቶ ነው። ቤተ ክርስቲያን ለአገር የሚጠቅም ተግባር ስትፈጽም ሳያውቋት የኖሩት ወገኖቻችን ቅድስናዋን እንዲረዱ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ ሲጨንቃቸው የተጠጓት መከራው ያለፈ ሲመስላቸው የምናጠፋት መስሏቸው መታገላቸውን ይጀምራሉ። በአገር ላይ መከራ ሲመጣ አበስኩ ገበርኩ በማለት ጥፋቱ የመጣው በእኔ ኃጢአት ነው የሚል አካል ባለመኖሩ እና ለአገር የሚጨነቅ በመጥፋቱ በጥፋት ላይ ጥፋት፣ በመከራ ላይ መከራ እየተፈራረቀ ያስጨንቀናል። ሁሉም ጣቱን የሚቀስረው ወደ ሌላ መሆኑ ችግሩ እንዲወሳሰብ እያደረገ ነው። እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች፣ በቅዱሱ አባት በኖኅ ዘመን እንደነበሩት ሰብአ ትካት ኃጢአት እየፈጸሙ ኃጢአት የሚናፍቃቸው እንጂ ንስሓ ገብተው ለጽድቅ የሚዘጋጁ አልታዩም። በሽታው ይሁን ጦርነቱ በእግዚአብሔር ቊጣ ባይመጣ እንኳ ጸሎት የማያርቀው ነገር ባለመኖሩ አጥብቆ በመጸለይ የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ የድርሻን መወጣት ይገባል። በአዲሱ ዓመት እገሌ ከእገሌ ሳንል ሁላችንም አስተሳሰባችንን በማስተካከል አገራችንን ለማልማት እንጂ ለማጥፋት ላለመሰለፍ መዘጋጀት፣ አምላካችን እንዲያግዘን መጸለይ ይኖርብናል።

ሕዝቡን ከእግዚአብሔር በመለየት ከቤተ ክርስቲያን አስኮብልለው በራሳቸው ዙሪያ እየሰበሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር እናገናኛችኋለን በማለት የሚቀልዱ ወገኖች የአገራችንም፣ የቤተ ክርስቲያንም ፈተናዎች መሆናቸውን መረዳት ይገባቸዋል። በስሙ የቀለዱት የደረሰባቸውን መጥፎ ግብር እየተናገሩ ዛሬም አንድ ጊዜ መድኃኔዓለም ለእገሌ ነገረው፣ ሌላ ጊዜ ለአባ እገሌ እንዲህ አለው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ በማለት መናገራቸው ያተረፈልን ግራ መጋባትን ነው። ጭንቅና መከራ ሲበዛ ክርስቶስ እዚህ አለ ቢሏችሁ እንኳ እንዳትቀበሏቸው በሚለው አምላካዊ ቃል ስንመራ ብንኖርም ሕይወታችን ባለመለወጡ ነቢያተ ሐሰት የተናገሩትን ሰምተን እንጨነቃለን። በልዩ ልዩ ስልት ሰውን የሚያስፈራሩ፣ በገሃነመ እሳት ትለበለባላችሁ የሚሉ የጥፋት መልእክተኞች ሕዝብ በማሸበር ደስታ ለማግኘት መሞከራቸው የታወቀ ቢሆንም ለአዲሱ ዓመት አዲስ ሰው ለመሆን እንሥራ። ኦርቶዶክሳውያንን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያንን የመጣው ሁሉ ወደ ፈለገው የሚነዳን ከሆንን ሰላማችን ይደፈርሳል፤ አንድነታችን ከአደጋ ላይ ይወድቃል። ጸንታችሁ ቁሙ የተባልነው በእንደዚህ ዓይነቱ የመከራ ዘመን ቢሆንም ፈርተው የሚያስፈሩ ብዙዎች ናቸው።

የፈራውን ወገናቸውን የበለጠ የሚያስጨንቁ፣ የሰውን ሰቆቃ ካልሰሙ ምግብ የማይበላላቸው የጥፋት መልእክተኞችን ዓላማ ልንረዳ ይገባል። ለሁሉ ነገር መፍትሔው በንስሓ ተመልሶ ቅዱስ ቊርባንን መቀበል፣ አምላካችን እንዲምረንም መማጸን

ነው:: እንዲህ እያደረግን ከአቅማችን በላይ የሆነውን ለአምላካችን ትተንና ምልክት ማየት ሳያሳስተን ሞት ቢመጣም ተዘጋጅተን እንጠብቅ:: በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ ሊያስፈርዱብን እንቅልፍ የሚያጡ ነቢያተ ሐሰትን፣ ክህናተ ጣዖትን እኛስ አምላካችንን እናውቀዋለን ከፊታችን ገለል በሉልን በማለት አሳፍረን ልንመልሳቸው ይገባል::

የበለጠ የሚጠቅመን ለዘመናችን የመከራ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በመለየት መንሥኤያቸውን ተረድቶ ችግሮችን በማስወገድ አገር ሰላም እንድትሆን፣ ሕዝብም እንዲረጋጋ ማድረግ ነው:: ከዓመት በፊት ኮሮና ቫይረስ ይበልጥ እንዳይሰራጭና ብዙ ሰው እንዳይጎዳ ከቤታችሁ ዋሉ፣ ከሰው አትገናኙ ተብሎ ቢታወጅ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሴት ልጆቻቸውን በመድፈር ሞት ሆይ ወዴት ነህ ብለው ሞተ ነፍስን የሚጠሩ መበርከታቸውን ከመገናኛ ብዙኃን ሰምተን ነበር:: አሁን ደግሞ ጦርነት ተጨመረ:: ጦርነቱ የእምነት ቦታዎችን ሆን ብሎ ማውደምንም ያካተተ ነው:: ድርጊቱ ከአምላክ በማጣላት ሰላም እንዲደፈርስ ያደርጋል እንጂ ለአጥፊው የሚጠቅመው ሆኖ አይደለም:: የሚጠቅመው የአምልኮ ቦታን ከመዳፈር መታቀብ ነው:: ሰዎች በሚፈጽሙት እኩይ ተግባር መከራው በመወገድ ፈንታ እየተስፋፋ፣ ጦርነቱ በመቀዝቀዝ ፈንታ እየከፋ፣ የእግዚአብሔር ቍጣ ወደ ትዕግሥት በመመለስ ፈንታ የበለጠ እንዲያጠፋን የሞትን ሾተል እየመዘዘ ነው:: ለዚህ ዋናው መድኃኒት ሁላችንም ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው::

በአንድ ወቅት ያልፈጸሙት የኃጢአት ዓይነት የለም የሚባልላቸው አንድ ሰው በአንድ አገር ይኖሩ ነበር:: ሰውዬው ዕድሜ የማያስተምራቸው፣ በሽታ መስመር የማያስገባቸው ነበሩ:: በዕድሜያቸው ላይ አንድ ቀን ቢጨመርላቸው ለድኅነት ሳይሆን ለጥፋት ለመጠቀም ለምኞታቸው ገደብ የሌላቸው ሰው ነበሩ:: ሲተኙ ክፋት፣ ሲነቁ ኃጢአት በዓይናቸው ይዞራል:: ለሰዎች የድኅነት ምክንያት የማያሳጣው አምላካችን እግዚአብሔር በአንድ ዕለት መልአከ ሞትን በገሃድ እንዲታያቸው ያደርጋል:: ሁል ጊዜ ኃጢአት የሚያየው ዓይናቸው የቤታቸውን በር ከፍቶ ወደ እሳቸው ከሚመጣ መልአከ ሞት ጋር ተገጣጠመ::

አመጣጡና ግርማው ያስፈራቸው አረጋዊም በደመ ነፍስ “አንተ ማን ነህ” በማለት እየተርበተበቱ ጠየቁት:: እርሱም “እኔ መልአከ ሞት ነኝ” ሲላቸው እየተንቀጠቀጡ “ለምን መጣህ?” አሉት:: እሱም “ኃጢአት ሠርተህ የማይበቃህ ሰው በመሆንህ ልወስድህ ነው” አላቸው:: ሽማግሌውም “ስላልተዘጋጀሁ እባክህ ተወኝ:: የአምላኬን ፊቱን እንዴት አየዋለሁ?” በማለት ወሸከቱ:: መልአከ ሞትም “አምላክህ ረጅም ዕድሜ ቢሰጥህም አትማርም:: የምታውቃቸው ከአጠገብህ በሞት ሲወሰዱ አልነቃህም:: መማር የማትፈልግ በመሆንህ ልወስድህ ነው” ሲላቸው “የዛሬን ተወኝ እንጂ ተዘጋጅቼ እጠብቅሃለሁ” አሉት:: እሱም “እንደማትማር ቢያውቅም አምላክህ አንድ ዕድል ሰጥቶሃል” በማለት ትቷቸው ሊሔድ መሆኑን ሲረዱ አረጋዊው ትንሽ ተረጋጉና ትንፋሻቸው መለስ ብላ “ተመስገን” አሉ::

እርሱም “ልብ አድርግ ከእንግዲህ ተመልሼ ስመጣ ሌላ ዕድል አልሰጥህም” አላቸው:: እሳቸውም “ከመምጣትህ በፊት አሳውቀኝ እንጂ ግድ የለም እዘጋጃለሁ በእኔ ይሁንብህ” ስላሉት ትቷቸው ሔደ:: ከጥቂት ቀናት በኋላ ከመኖሪያ ቤታቸው ራቅ ካለ ቦታ ሰው መሞቱን ሲሰሙ “ወይ ጉድ” ብለው እኔንስ “ሳልነግርህ አልወስድህም ብሎኛል” በማለት ጥፋታቸውን ቀጠሉ:: በመቀጠልም ከቤታቸው ቀረብ ካለ ቦታ አንድ ሰው ወሰደ:: እሳቸውም አይጉድ ብለው በቀደመ የጥፋት ግብራቸው ቀጠሉ:: አሁንም ቀረብ ብሎ ወዳጃቸውን ወሰደ፤ ከዚያም ልጃቸውን ሲወስድ አልቅሰው ወደ ኃጢአት ተመለሱ:: ከዚያ ሚስታቸውን ወሰደ:: ሌሎችን ሲወስድ ይማራሉ ብሎ ቢጠብቃቸው ወይ ፍንክች አሉ::

መጨረሻ ላይ የቤታቸውን በር ከፍቶ ሲገባ ደነገጡና “አንተ ማን ነህ?” ሲሉት “እኔማ መልአከ ሞት ነኝ” አላቸው:: “ሳልነግርህ አልመጣም ብለኸኝ እኮ ነበር” አሉት:: እሱም “ከዚያ ማዶ ጀምሬ ሰው ስወስድ ተዘጋጅ ማለቴ ነበር:: አንተ ግን ባለፈው እንደነገርኩህ ኃጢአት እየጣፈጠህ ስለሔደ ከዚህ በላይ ዕድሜ ቢጨመርልህም አትማርም:: ተጨማሪ ሰዎችን ሳትጎዳ ልውሰድህ” ብሎ አንቆ ወሰዳቸው:: በዚህ ዘመንም ኃጢአት ሲርባቸው የኖሩትን አረጋዊ የሚመስሉ ብዙ ሰዎች አሉ:: ወደ እሱ እንዲመለሱ አምላካችን እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ምልክቶችን ቢያሳያቸውም ከእሱ የሚያርቃቸውን እንጂ ወደ እሱ የሚያቀርባቸውን በጎ ተግባር መፈጸም አልቻሉም:: የንስሓ ዕድሜ ሲሰጣቸው በኃጢአት ላይ ኃጢአት እየደረቡ አምላካቸውን የሚፈታተኑ ወገኖቻችን ቍጥር ከመቀነስ ይልቅ እየበዛ ነው:: ከልቡ ታገሥኩ ተመለስኩ የሚል ባለመኖሩ የመከራው ጊዜ እየተራዘመ መሔድ ብቻ ሳይሆን ሌሎች አስጨናቂ ነገሮችም ለመከሠት ምልክቶች እየታዩ ነው::

ብዙዎቻችን እየሠራን ያለነው እግዚአብሔር ምሕረት እንዲያወርድ የሚያደርግ ሳይሆን “አሕዛብስ ቤተ አይሁድ ካደረጉት የከፋ ምን አደረጉኝ” በማለት ለሰባ ዓመታት በባቢሎን እንዲማረኩ አድርጉ አሳራቸውን እንዲያዩ ያደረጋቸውን እስራኤላውያንን ኃጢአት የሚያስንቅ ነው:: “እግዚአብሔር በሰጣቸው የመንግሥት አስተዳደር ላይ የቸልታ መንፈስ ቢያመጡ፣ ሕጉን ቢለውጡ፣ ወሰን ክልላቸውን፣ ትምህርተ ሃይማኖታቸውን ባይጠብቁ፣ የአምላካቸውን እና የአገራቸውን ክብር ቢንቁ፣ ፍርድ ቢያደሉ፣ መማለጃ ቢበሉ፣ በቤተ መንግሥት፣ በቤተ ክህነት የሚሠራውን ግፍ እንዳያዩ ዐይናቸውን ቢሸፍኑ፣ የድሆችን ጩኸት እንዳይሰሙ ጆሮዋቸውን ቢደፍኑ፣ የግል ጥቅማቸውን ፈላጊዎች፣ መብል መጠጥ ወዳጆች ቢሆኑ፣ የእግዚአብሔርን አደራ ቢያቃልሉ፣ አፈ ጻድቅ መስለው በልቡናቸው ቢክዱ፣ በእርሱ ላይ የሰው ወይም የጋኔን ውሽማ ይዘው ጉድን ጉድን ቢሔዱ፣ ከቤት ወይም ከጎረቤት ጠላት አስነሥቶ ያስደነግጣቸዋል፤ ያንቀጠቅጣቸዋል:: ከክብራቸው፣ ከቤታቸው ያወጣቸዋል:: በደዌ፣ በጦር፣ በረሃብ፣ በቸነፈር፣ በስደት፣ በሞት ይቀጣቸዋል” (አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ፲፱፶፩÷ገ፲፴) በማለት ሊቁ የተናገሩት እየተፈጸመ በመሆኑ ወደ አምላካችን እንመለስ::

መልአከ ሞት ከዚህ በላይ እንዴት ልታገሥህ በማለት ተማሮ ሊቆርጠን እንዲመጣ የሚያደርገው ኃጢአትን ባለመጥገብ

በጥፋት ላይ ጥፋት ለመፈጸም ስንነሣሣ ነው። ስንሓ እንድንገባ በወገኖቻችን ሞት ቢነግረንም አልሰማንም። ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ሥልጣን፣ ሀብት እና ሌላም ቊሳዊ ነገር ከማያግደው በሽታ የበለጠ፣ ዓለምን ካለ ሰው ከሚያስቀር ጦርነት የበለጠ መምህር ሊመጣልን እንደማይችል ተረድተን ለወገኖቻችን የመከራ ምንጭ ከመሆን የሰላም መልእክተኛ ለመሆን ንስሓ እንግባ። እንደ ነዌ ከሙታን ተነሥቶ ያልመጣ ካላስተማረን አንመለስም እያልን በኃጢአት ላይ ኃጢአት እየፈጸምን በመሆኑ ኃጢአት መሥራት አንገሽግሾን የእግዚአብሔርን ምሕረት እንለምን። ማርያም እንተ ዕፍረት ኃጢአት አማናዊውን ደስታ እንደማያስገኝ ተረድታ ወደ ክርስቶስ ስለቀረበች ስሟ ወንጌል በተነበበበት ሁሉ ሲጠራ ይኖራል። አመንዝራዎች ግን ስማቸው በአንድ ትውልድ ይጠፋል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሰሙነ ሕማማት ጸሎቷ "በዚች ቦታና በሌሎችም ቦታዎች ስለሚገኙ፣ በነፍስ በሥጋ ስለታመሙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ ለእኛም፣ ለእነሱም ጤንነቱን ሰጥቶ በጎ ነገርን ያደርግልን ዘንድ፤ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ፤ በባሕር፣ በየብስ፣ በቀላይ፣ በአየር በሌላም መንገድ ሁሉ ስለሚጓዙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ በቀና መንገድ መርቶ በሰላም፣ በደስታ ወደ መኖሪያቸው ይመልሳቸው ዘንድ፣ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ። ከእርሻ ስለሚገኝ ፍሬ፣ ስለዛፎችና ስለወይኖች፣ በዓለም ፍሬን ስለምታፈራ እንጨት ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ፣ አብዝቶ፣ ከጥፋትም ጠብቆ ለፍጻሜ ፍሬ ያደርሳቸው ዘንድ፣ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ። አምላካችን ክርስቶስ በገዥዎችና በፈራጆች ፊት ይቅርታንና ምሕረትን እንዲሰጠን፣ ልቡናቸውንም ሁል ጊዜ በቸርነቱ እንዲያራራልን ጸልዩ። የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ" (ግብረ ሕማማት ፲፱፻፺፮፥፻፰-፻፱) በማለት ትጸልያለች።

ይህ ብቻ ሳይሆን "በክርስቶስ አምነው ከዚህ በፊት ስለሞቱ ወንድሞቻችንና አባቶቻችን ጸልዩ። እነሱም፦ የተቀደሱ አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳትና አባቶቻችን ጳጳሳት፣ አባቶቻችን ኤጲስ ቆጶሳት፣ አባቶቻችን ቆሞሳት፣ አባቶቻችን ካህናት፣ ወንድሞቻችን ዲያቆናት፣ አባቶቻችን መነኰሳትና አባቶቻችን ሕዝባውያን፣ ሌሎችም ከክርስቲያን ወገን በሞት ያረፉት ሁሉ ናቸው። ጌታ ዕረፍተ ነፍስን ይሰጣቸው ዘንድ ጸልዩ። የክርስቲያን እምነት ላልተፈጸመላቸው ወገኖች ጸልዩ። ጌታ ይባርካቸው ዘንድ፣ እስከ መጨረሻዪቱም ሕቅታ በቀናች ሃይማኖት ያጸናቸው ዘንድ፣ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ …" (ግብረ ሕማማት ፲፱፻፺፮፥፻፰-፻፱) በማለት ስለሰው ልጆች ሁሉ ወደ ፈጣሪዋ ዕለት ዕለት ታሳስባለች። አመኑም አላመኑም ስለ መንግሥታት የምትጸልየው ለፍጥረታት ሁሉ ድኅነት ስለምታስብ ነው። አሁን ባለንበት ዘመን እንዲህ ብሎ መጸለይ ከቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ከክርስቲያኖች ሁሉ የሚጠበቅ ተግባር ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት በአንድ በኩል እኛ ኃጢአትን በጽድቅ ለማሸነፍ ትንሣኤ ልቡና እንዲኖረን ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለሚደግፏት ብቻ ሳይሆን ለሚገፏትም አጥብቃ ፈጣሪዋን የምትማጸን ፍጽምት መሆኗን እንድንረዳ ዓይነ ልቡናችንን ያበራልናል። በአጸደ ነፍስ ላሉት ሳይቀር ጸሎት የማያስፈልገው ቅዱስ አለመኖሩንም ያስገንዝበናል። በዐሪ ላይ ቆመው ቤተ ክርስቲያን እንድትዘጋ የሚያደርጉትንም በፍቅሯ ማሸነፍ እንደምትችል አምና ዕለት ዕለት መሠረቷና ጉልላቷ ወደ ሆነው ክርስቶስ ታሳስባላቸዋለች። በቃል መናገር ብቻ ሳይሆን የተናገረችውን በተግባር ፈጽማ ታሳየናለች። "ይህ ዓይነት አብሮ አደግ ጋኔን ካለጾምና ካለጸሎት አይወጣም" (ማቴ.፲፯፥፳፩) ተብሎ በቅዱስ ወንጌል እንደተነገረው በአገራችን የተከሠተው ችግር ያለጸሎት ስለማይከስም እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን የአምላካችንን ምሕረት መማጸን ሲገባን እባክህ ፈጥነህ አጥፋን ብለን መገዳደር የጀመርን አስመስሎብናል።

"የሆድህ ፍሬ፥ የምድርህም ፍሬ፥ የላምህም ርቢ፥ የበግህም ርቢ ርጉም ይሆናል። አንተ በመግባትህ ርጉም ትሆናለህ፥ በመውጣትህም ርጉም ትሆናለህ። እኔን ስለ ተውኸኝ፥ ስለ ሥራህ ክፋት፥ እስክትጠፋ ፈጥነህም እስክታልቅ ድረስ በምትሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር መርገምን፥ ሽሽትን፥ ተግሣጽን ይሰድድብሃል። እግዚአብሔር ትወርሳት ዘንድ ከምትገባባት ምድር እስኪያጠፋህ ድረስ ቸነፈርን ያጠብቅብሃል። እግዚአብሔር በክሳት፥ በንዳድም፥ በጥብሳትም፥ በትኵሳትም፥ በድርቅም፥ በዋግም፥ በአረማሞም ይመታሃል፤ እስክትጠፋም ድረስ ያሳድዱሃል። እግዚአብሔር በዕብደት፥ በዕውርነት፥ በድንጋጤም ይመታሃል"(ዘዳ፳፰፥፲፩-፳፰) ተብሎ የተነገረው ተፈጽሞብን መዘባበቻ እንዳንሆን እንጠንቀቅ።

በቴሌቪዥን፣ በጡመራ መድረክ፣ በዩቲዩብ ቃለ እግዚአብሔር ሲተላለፍ አእምሯችንን ሰብስበን ከማዳመጥ ይልቅ በየማኅበራዊ ሚዲያው በሚደመጡ ዋልታ ረገጥ አሳቦች በመጨቃጨቅ ጊዜያችንን እናሳልፋዋለን። የሚያረጋጋን ለሌሎች ብለን መስማት ሳይሆን ለራሳችን ብለን መስማት ነው። ትምህርቱንም፣ ጸሎቱንም አእምሯችንን ሰብስበን እንከታተል። ቀስ በቀስ የምንሰማው ቃለ እግዚአብሔር ራሳችንን እየለወጠን ይሔዳል። የተቸገሩትን ለማረጋጋት የሚያስችል አቅም ያላቸው እየተሸበሩ ሌሎችን ላለማሸበር ስሜታቸውን ቢቈጣጠሩ መልካም ነው። አምላካችን መጽናናቱን እንዲሰጠን እየተማጸንን አምላካችን እግዚአብሔር የሚያደርገውን በትዕግሥት እንጠብቅ። በሌሎች መፍረድን ትተን የምንችለውን እንሥራ።

በዘመናችን የተከሠተው መከራ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድንቀርብ እንጂ ከቤተ ክርስቲያን የምንርቅበት ባለመሆኑ መክሊት እንዲገለጥ፣ ከእንቅልፍ እንድንነቃ እግዚአብሔር ያመጣው ከኃጢአት መመለሻ ጨንገር መሆኑን አምነን ወደ ጽድቅ እንመለስ። መከራ እና ፈተና ለጽድቅ የምንበቃበትን በጎ ነገር የምንሠራበት እንጂ ወደ ጥፋት የምንነዳበት መሆን የለበትም።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፣ ወለወላዲቱ ድንግል፣ ወለመስቀሉ ክቡር። አሜን!! ☩

# "መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ"

(ዕብ.፲፫÷፲፮)

ዲ/ን ተስፋዬ ምትኩ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ በክርስቶስ ክርስቲያን፣ በወልድ ውሉደ እግዚአብሔር፣ በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳውያን የተሰኙ ምእመናን አኗኗራቸው ምን መምሰል እንዳለበት ሲናገር "መልካም ማድረግን፣ ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና" (ዕብ.፲፫÷፲፮) ብሏል። ለመሆኑ መልካም የተባለው ነገር ምንድን ነው? መልካም ማድረግና ለሌሎች ማካፈልስ እንዴት ነው? የሚለው በዚህ ጽሑፍ በስፋት የምንመለከተው ርእሰ ጉዳይ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሕይወቱ መምህሩን ክርስቶስን የመሰለ እና ለምእመናንም እኔን ምሰሉ ብሎ ለመናገር የበቃ ታላቅ መምህር ነው። "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" (፩ኛቆሮ.፲፩÷፩) በማለት ያስተማረው ክርስቶስን መምሰል ጥቅም እንጂ ጉዳት ስለሌለው ነው። ክርስቶስ በዚህ ምድር የሠራው ሁሉ ለእኛ መልካም ምሳሌ ለመሆን ነውና እኛም ክርስቲያን ተብለን በስሙ እስከተጠራን ድረስ በስም ብቻ ሳይሆን በአኗኗራችንም እርሱ የተናገረውንና ያከናወነውን መልካም ነገር ሁሉ በተግባር በመፈጸም ልንመስለው ይገባናል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ሲያስተምር አንድ ሰው ወደ እርሱ ቀርቦ "መምህር ሆይ፥ የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ?" ብሎ ጠይቆት ነበር። ጌታም "ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ" በማለት መልሶለታል። ሰውዬው ጥያቄውን በዚያ አላቆመም "የትኞቹን" ሲል ደግሞ ጠየቀው። ጌታም "አትግደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ" (ማቴ.፲፱÷፲፯-፲፱) በማለት ዐሠርቱ ሕግጋተ ኦሪትን ዘርዝሮለታል።

"መልካም የሆነው አንድ ነው፤" የሚለውና "ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትእዛዛቱን ጠብቅ" የሚሉት አሳቦች መልካም የተባለው ሕገ እግዚአብሔር መሆኑንና መልካም ማድረግ የተባለውም ሕገ እግዚአብሔርን መፈጸም መሆኑን ያስገነዝቡናል። እግዚአብሔር በባሕርዩ መልካም ነው። ከመልካምነት ውጭ እግዚአብሔርን ማሰብም ሆነ ማወቅ አንችልም። አሳቡም፣ ሥራውም፣ አጠቃላይ ባሕርዩም መልካምነት ነው። ሕግጋቱና ትእዛዛቱም መልካም ናቸው። መልካምነትን ገንዘብ ያደረጉ ሰዎች ደግሞ ሕግጋቱን ይጠብቃሉ፤ ትእዛዛቱንም እየፈጸሙ እንደፈቃዱ ይመላለሳሉ።

ያለንን ማካፈል ስንል ብዙ ጊዜ ትዝ የሚለን፣ የዕለት ጉርስ፣ የዓመት ልብስ ላጡትና ለተቸገሩት ሰዎች ቆርሶ ማጉረስን፣ ቀዶ ማልበስን ነው። ይህ ተገቢና አስፈላጊ ነው። ጌታም ይህንኑ እንድናደርግ አስተምሮናል። ለፍርድ በሚመጣበትም ጊዜ ጻድቃንን "የአባቴ ቡሩካን ወደ እኔ ኑ" ብሎ የሚፈርድላቸው፣ ኃጥአንን ደግሞ "ከእኔ ሒዱ፤ ወግዱ" ብሎ የሚፈርድባቸው በአጠገባቸው ያሉትን ድሆች መርዳታቸውን እና አለመርዳታቸውን ወይም ትእዛዛቱን መፈጸም አለመፈጸማቸውን መሠረት አድርጎ ነው። ይህን ስንል ግን የምንጸድቅበትና የምንኰነንበት ዋናውና ብቸኛው ምክንያት ይህ ነው ማለት አይደለም። ዋናው ሃይማኖት ነው፤ ከሃይማኖት ምግባር ይከተላል፤ ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ፣ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖርም ሰውን ወደ ጽድቅ ከሚመሩ ነገሮች ዋነኞቹ ናቸው። ማካፈልም የሚገባን በዋናነት እነዚህን ነው። የመንፈሳዊነት መሠረቱ እነዚህ ናቸውና።

## ሀ. ሃይማኖትን ማካፈል

ሃይማኖት መሠረት ነው። ምግባር ትሩፋት ደግሞ ግድግዳና ጣሪያ ናቸው። ቤት መሥራት የሚጀምረው ከመሠረት ነው። መሠረት ሳይኖር ግድግዳና ጣሪያ መሥራት አይቻልምና። ለመሥራት ቢታሰብ እንኳ ጸንቶ አይቆምም። ምክንያቱም ንፋስ ቢነፍስ አሊያም ጎርፍ ቢመጣ ያፈርሰዋልና (ማቴ.፯÷፳፯)። ለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያናችን ምግባር ትሩፋት መሥራትን ከማስተማሯ በፊት ሃይማኖትን የምታስተምረው። መሠረት የሌለው ቤት አይቆምም። ሃይማኖት ሳይኖረን መልካም ሥራ መሥራትም ብቻውን ሰማያዊ ዋጋ ሊያሰጠን አይችልም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን አስመልክቶ "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቀድሞ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጣቸው ሊያምን ይገባዋል" (ዕብ.፲፩÷፯) በማለት የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራል።

የመልካምነት ምንጩ እግዚአብሔር ነው። ስለሆነም መልካምነትን ገንዘባችን ለማድረግ መልካምነት የባሕርይ ገንዘቡ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ሊኖረን ይገባል። የእግዚአብሔር ልጆችና ወዳጆች የምንሆንበት ምሥጢር ደግሞ ሃይማኖት ነው። እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ ቢሆንም አባትነቱ

ግን ወደው ፈቅደው ለተቀበሉት ብቻ ነውና፡፡ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" (ዮሐ.፩፥፲፪) ተብሏልና፡፡ ስለሆነም ህልወተ እግዚአብሔርን አምነን፣ በስመ ሥላሴ ተጠምቀን፣ በወልድ ውሉደ እግዚአብሔር ለመሆን የታደልን ምእመናን ይህን ዕድል ያላገኙትን ወገኖች ከእኛ ጋር አንድ እንዲሆኑ የክርስትናን ምንነትና የክርስቶስን ማንነት፣ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን ምሥጢር ልናስተምራቸው (ልናካፍላቸው) ይገባል፡፡

## ለ. በጎ አርአያ መሆን

አርአያ መሆን ሲባል በዕለት ተዕለት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወታችን ሁሉ ሰውንና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መልካም ነገርን በማድረግ በመልካም ሕይወታችን፣ በበጎ ምግባራችን ሌሎችም በጎ ነገር እንዲሠሩ ማድረግ ነው፡፡ ይህም በጎነትን ለሌሎች ማካፈል ወይም አርአያ መሆን ነው፡፡ በጎ አርአያነት በአንድ ማኅበረሰብ ወይም ተቋም ተቀባይነትን ያገኘ፣ የተወደደ እና የተለመደ ባህልንም ያመለክታል፡፡ በማኅበረሰብ ውስጥ እየኖረ ከማኅበረሰቡ ልማድና ሥርዐት ውጭ የሆነ ግለሰብ ቢገኝ ማኅበረሰቡ አንተ እኛን ስለማትመስል ከእኛ ጋር መኖር አትችልም ብሎ ስለሚለየው ባይተዋር መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ዐልፎ ተርፎም፣ ከምግባሩ ብልሹነት የተነሣ ይናቃል፤ ይተቻል፤ ይገፋል፤ ይገለላልም፡፡ ምክንያቱም ማንነቱ ኅበረተሰቡን አይወክልምና፡፡ እንደ ክርስትና መልካም ምግባር ስንል ሕግጋተ እግዚአብሔርን ይመለከታል፡፡ እንደ ክርስትናም የበጎ ምግባር መሠረቱ እግዚአብሔር አታድርጉ ያለውን መተው፣ አድርጉ ያለውንም መፈጸም ነው፡፡

ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ሕግ የማይጻረር እስከ ሆነ ድርስ የማኅበረሰብን ወግና ልማድ አብረው ይሳተፋሉ እንጂ አይቃወሙም፡፡ የመሳተፋቸው ዋና ዓላማም የማኅበረሰቡን ልማድ ለመካፈል ብቻ አይደለም፤ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ክርስቲያናዊ ምግባራትን ለማኅበራሰባቸው ለማካፈል ጭምር እንጂ፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ሌሎችን ወደ እውነተኛው የሕይወት መንገድ ለመመለስ ሲሉ ከክርስቲያናዊ ሕይወታቸው የሚጣረስ የመሰለ ተግባር ጭምር እስከ መሥራት የሚያደርስ መሥዋዕትነትን ይከፍላሉ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን እውነት ሲናገር፡- "እኔ ከሁሉ ይልቅ ነፃ ስሆን ብዙዎችን ወደ ሃይማኖት እሰበስባቸው ዘንድ እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛሁ፡፡ አይሁድን እጠቅማቸው ዘንድ ለአይሁድ እንደ አይሁዳዊ ሆንሁላቸው፤ ከኦሪት በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ፥ ራሴ ከኦሪት በታች ሳልሆን፥ ከኦሪት በታች ላሉት ከኦሪት በታች እንዳለ ሰው ሆንሁላቸው፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጋሁ ሳልሆን በክርስቶስ ሕግም ሳለሁ፥ ሕግ የሌላቸውን እጠቅም ዘንድ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደ ሌለው ሆንሁላቸው፡፡ ደካሞችንም እጠቅማቸው ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁላቸው፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶቹን አድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ፡፡ በወንጌልም ትምህርት አንድነት ይኖረኝ ዘንድ ስለወንጌል ትምህርት ሁሉን አደርጋለሁ" (፩ኛ ቆሮ.፱፥፲፱-፳፫) ብሏል፡፡

## ሐ. ሰላምን ማካፈል

ሰላም ከሌሎች ጋር በስምምነትና በአንድነት አብሮ መኖር ማለት ነው፡፡ ሰላም የዕረፍት፣ የደስታ፣ የጸጥታና የርጋታ ስሜት ነው፡፡ ሰላም የሰው ልጅ በዚህ ምድር ለመኖር እጅግ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ያለ ሰላም ወጥቶ መግባት፣ ሠርቶ መብላት፣ የአእምሮ ርካታና የልብ ደስታ ማግኘት አይቻልም፡፡ የሰው ልጅ የዚህን ምድር ኑሮ እንዲሰለች በመንፈሳዊው ሕይወትም ተስፋ እንዲቆርጥ የሚያደርገው ዋነኛው ጉዳይ ሰላምን ማጣቱ ነው፡፡

ሰላም መሆን ስንል ከሦስት ነገሮች ጋር ነው፤ ማለትም ከራሳችን ጋር፣ ከእግዚአብሔር ጋር እና ከሌሎች ሰዎች ጋር ሰላም መሆን ይጠበቅብናል፡፡ የሰው ልጅ እንስሳዊ የሆነ ጊዜአዊ ስሜት፣ የሚያስተውል አእምሮ እና አሳብን እና ድርጊትን ሁሉ መልካም ነው ወይስ ክፉ እያለ የሚያመዛዝን ሕሊና ያለው ፍጥረት ነው፡፡ ስለሆነም ከራሳችን ጋር ሰላም መሆን ስንል ለሕሊና ወቀሳ የሚጋብዘንን፣ አእምሯችንን የሚረብሸንን ሥራ ከመሥራት መቆጠብ ይጠበቅብናል ማለታችን ነው፡፡ ተሳስተን ኃጢአት ብንሠራ እንኳ በንስሓ መመለስ ይኖርብናል፡፡ ከራስ ጋር ሰላም መሆን እያልን ያለነውም ይህንን ነው፡፡ ሁለተኛው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆን የሚለው ሲሆን ይኸውም ለሕግጋተ እግዚአብሔር መገዛትን የሚመለከት ነው፡፡የእግዚአብሔር ቃል "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" ነውና የሚለው ትእዛዛቱን ጠብቀን ከእርሱ ጋር በፍቅር ከኖርን ሰላም ይኖረናል፡፡ ሦስተኛውና ካነሣነው ርእሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታ የሚገናኘው ደግሞ ከሰው ሁሉ ጋር ሰላም መሆን የሚለው ነው፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ … ክፉን በመልካምሥራ ድል ንሣው እንጂ ክፉን በክፉ ድል አትንሣው" (ሮሜ.፲፪፥፲፰-፳፩) በማለት ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም እንድንኖር መክሮናል፡፡ እዚህ ላይ ከሰው ሁሉ የሚለው ዘር፣ ቀለም፣ የኑሮ ደረጃ እና አስተሳሰብ፣ እምነትና አመለካከት ወዘተ መስፈርት አድርገን ሳንገድብ ከሁሉ ጋር መስማማት እንደሚገባን ያስገነዝበናል፡፡ ይህን ስንል ከመንፈሳዊ ግባችን ጋር የማይስማማ አመለካከትና አኗኗር ያላቸውን ሰዎች በክፉ ሥራቸው መተባበር አለብን ለማለት አይደለም፡፡ ከቻልን ወደ እውነተኛው የሕይወት መንገድ እንዲመጡ በምክር፣ በጸሎት እና በመልካም ምሳሌነት ማገዝ፣ ይህን ማድረግ ባንችል እንኳ ለጠብ ከሚያነሣሡ ነገሮች ተቆጥበን በመከባበር እና በመቻቻል ላይ በተመሠረተ ሕይወት መኖር ነው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ወደ ሰማይ /ወደ ቀደመው ክብሩ/ እንደሚመለስ በነገራቸው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ለማን ጥለኸን ትሔዳለህ ብለው መከፋታቸውን ተመልክቶ "ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜንም እሰጣችኋለሁ" በማለት አጽናንቷቸዋል፡፡ ይህንም ሲል እኔ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ አልለያችሁም ማለቱ ነው፡፡ ከዚህም በኋላ ሰላሙ ፍጹም መሆኑን ሲናገር "እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም" (ዮሐ.፲፬፥፳፯) ብሏል፡፡

ታዲያ ከሌሎች ጋር በሰላም ለመኖር ይህን ፍጹም ሰላም ለሌሎች ከማካፈል የበለጠ ምን መልካምነት ይገኛል? ዛሬ ዓለም ሰላም ኀድሎታል፡፡ ወጥተው መግባት፣ ሠርተው መብላትና ሌሎችንም ሰላማዊ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን ያቃታቸው በርካቶች ናቸው፡፡ ሰላም ከሰው ልጆች ከመራቁ የተነሣ ቤት ያፈራውን አብስለው መመገብ ባለመቻላቸው የሚራቡ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ለብዙ ሰው የሚበቃ ሀብትና ንብረት እያላቸው አንዱ አንዱን ለማጥፋት ዕንቅልፍ የሚያጡ የቃየል የግብር ልጆች በዝተዋል፡፡ ለእነዚህ ሁሉ የሰላሙን ምንጭ ክርስቶስን ልንሰብክላቸው፣ የሰላም ሕይወት የሆናቸውን ክርስትናን ልናካፍላቸው ይገባል፡፡

## መ. ፍቅርን ማካፈል

ፍቅር የመንፈስ ፍሬ፣ የሃይማኖት መሠረት እና የንጹሕ ልብ ምልክት ነው፡፡ ፍቅር የበጎ ሥራ ምክንያት፣ የመተሳሰብና የደግነት ምንጭ በመሆኑ የመንፈሳዊ ሰው ዋናው እና አቻ የማይገኝለት መገለጫው ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፍቅር የመንፈሳዊነት መገለጫዎችን ሁሉ አጣምሮ መያዝ እንደሚችል ሲናገር "ፍቅር ያስታግሣል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር አያቅናናም፤ ፍቅር አያስመካም፤ ፍቅር አያስታብይም፡፡ ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም፤ አያበሳጭም፤ ክፉ ነገርን አያሳስብም፡፡ ጽድቅን በመሥራት ደስ ያሰኛል እንጂ፡፡ ግፍ በመሥራት ደስ አያሰኝም፤ በሁሉ ያቻችላል፤ በሁሉም ያስተማምናል፤ በሁሉም ተስፋ ያስደርጋል፣ በሁሉም ያስታግሣል" (፩ኛቆሮ.፲፫፥፬-፯) በማለት ፍቅር የመልካም ምግባራት ሁሉ ራስ መሆኑን ገልጾታል፡፡

የሰው ልጆችን በዋናነት የሚያጣሏቸው፣ እንደ ውሻም እርስ በእርስ የሚያናክሷቸው ጥቅም ቀረብኝ፣ ተበደልኩ፣ ክብሬ ተነካ፣ ተዋረድኩ ወዘተ. የሚሉ የሥጋዊ ጥቅምና ክብር ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህ በሐዋርያው መልእክት ላይ ደግሞ ፍቅር "ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም፤ ክፉ ነገርን አያሳስብም" የሚሉ ቃላት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ የእውነተኛው ፍቅር መገለጫዎች ናቸው፡፡ የራሱ መሆኑን እያወቀ አሳልፎ ለሌላ የሚሰጥ እና በደልን የማይቈጥር፣ ለክብሩም የማይጨነቅ ሰው በምንም ምክንያት ከሰው አይጣላም፡፡ ቅዱሳን አባቶች ይህን በተግባር ፈጽመውታል፡፡

ዛሬ በዓለማችን ብዙ በፍቅር ስም የሚጠሩ ነገር ግን እውነተኛውን ፍቅር የማይወክሉ ነገሮች አሉ፡፡ እውነተኛ ፍቅር ግን ክርስቶስ ዓለምን የወደደበት ፍቅር ብቻ ነው፡፡ የክርስቶስ ፍቅር በዝምድና፣ በውለታና በስጦታ ላይ ያልተመሠረተ ንጹሕ ፍቅር ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ይህን ሲናገር ነው "ዓለምን እንዲሁ ወድዶታልና" (ዮሐ.፫፥፲፮) ያለው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ "እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ይቅር ካለን ከታረቀን በኋላም በልጁ ሕይወት እንዴት የበለጠ ያድነን" (ሮሜ፭፥፲)ብሏል፡፡ ዛሬ ዓለማችን ላይ ያለው ፍቅር ግን በደም /በዝምድና/ እና በውለታ በአጠቃላይ በጊዜያዊ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ፍቅር የቃልና የአንደበት እንጂ እውነተኛ ስላልሆነ የመንፈሳዊነት መገለጫ ሊሆን አይችልም፡፡

"እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይሁንባችሁ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና፡፡ አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፣ በውሸት አትመስክር፣ አትመኝ የሚሉት ትእዛዞች ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልለዋል፡፡ ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም ስለዚህ ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነው" (ሮሜ፲፫፥፰-፲)እንዲል፡፡

በአጠቃላይ "መልካም ማድረግን፣ ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ" በማለት ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን በሐዋርያው ትምህርት ጸንተን መልካም ነገሮች ናቸው ብለን ከላይ የዘረዘርናቸውን ሃይማኖትን፣ በጎ ምግባርን፣ ሰላምን እና ፍቅርን አጽንተን መያዝ ይኖርብናል፡፡ እነዚህን ነገሮች ለእኛ ብቻ እንድንኖራቸው ሳይሆን ለሌሎችም እንድናካፍላቸው ተነግሮናል፡፡ ደግሞ "ያለው ለሌለው ይስጥ" የሚለው የቅዱስ ወንጌል ትምህርት ሥጋዊ ፍላጎትን የሚያሟሉትን ነገሮች ብቻ ሳይሆን ዘለዓለማዊ ርስትን የሚያወርሱትን ሁሉ ነውና እነዚህን በጎነቶች ለእኛ አጽንተን መያዝ፣ ለሌላውም ማካፈል ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ሁሉ ደግሞ እግዚአብሔር ሲፈቅድ ነውና ሃይማኖትን፣ በጎ ምግባርን፣ ሰላምን እና ፍቅርን እኛ ኑረንባቸው ለሌላውም አካፍለን የመንግሥቱ ወራሾች፣ የስሙ ቀዳሾች እንድንሆን የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ሁሉ ተራዳኢነት አይለየን፡፡ አሜን!! ⌖

"መስቀል ቤዛነ ፀወንነ መድኃኒተ ነፍስነ ለእለ አመነ ምክሐ ሰላምነ ዘይሠሪ ኃጢአተነ መስቀል ኮነ ሕይወተ፡- መስቀል ቤዛችን፣ መጠጊያችን፣ ለነፍሳችን መድኃኒት፣ ላመንን የሰላማችን መመኪያ፣ ኃጣአታችንንም ይቅር ብሎ ሕይወትን የሚሰጥ ሆነ"፡፡

ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ

# ዚኖቢስና ዚኖቢያ

ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን

በአውግስጦስ እና በቀላውዴዎስ ቄሣር ዘመነ መንግሥት ሉቅያኖስ ኤጌዎን በተባለች አገር ገዥ በነበረበት ጊዜ በክርስቲያኖች ላይ ጽኑ ስደት ጸፈጸመ። ቈስጠንጢኖስ የተባለ ጸሐፊ ንጉሡን ንጉሥ ሆይ ሺሕ ዓመት ንገሥ ባይስ በተባለ ሀገር አንድ ሰው አለ። አባቱ እና እናቱ ሥርዓታቸው የተለየ ታላላቅ ሰዎች ናቸው። ክርስቲያኖች መሆናቸውን እንጠጥራለን አለው። አረማውያንን ወደ ክርስትና ሃይማኖት ያስገባቸዋል። ወፍ ሳይንጫጫ በሌሊት ያስወጣቸዋል። በዕለቱም ብዙዎች ወደ እነርሱ በመሔድ ክርስቲያን ይሆናሉ። ወገኖቻችንን ሁሉ ክርስቲያን የሚያደርጓቸውን ሰዎች አስረው ያመጧቸው ዘንድ ጠንካራ ወታደሮችን ላክ አለው። ንጉሡም አጳርጎሪስን ጥሩት አለ። ወታደሮቹም ከዚህ ቆሟል አሉት። ንጉሡም ብርቱ ሰዎችን ላክ፤ የሚያሳያቸውን ይያዙና አስረው ወደ እኔ ያምጧቸው። ፈቃደኛ የማይሆን ካለና ልጇ በመወሰዱ እናቱ ካለቀሰች እርሷንም አስራችሁ አምጧት አላቸው።

ወታደሮችም እንደታዘዙት ዚኖቢስንና ዚኖቢያን አመጡለት። ገዢውም ዚኖቢስን ሥርዓትህ ምንድን ነው? ወገንህስ ከማን ነው? ይህን የምታደርግ አንተ ሀገርህ የት ነው? በዚህ ሀገር የሚኖሩትን ሰዎች ክርስቲያን እንደምታደርጋቸው ሰምቻለሁ አለው። ዚኖቢስም ሃይማኖቴን ማወቅ ከፈለግህ ክርስቲያን ነኝ። በሁሉም የምታወቅበት ስሜም ዚኖቢስ ነው። አገረ ገዢ ነበርሁ። በኋላ ስደት ሆነና ከወዳጆቼ ጋር ተሰደድን፤ በሮም ብዙ የሚያውቁኝ ሰዎች አሉ።

ለዘለዓለሙ ይድኑ ዘንድም ብዙዎች ተሰብስበው በመማር ክርስቲያን ይሆናሉ። የክርስቲያንነት ምልክት የሆነውን ማዕተብም ይወስዳሉ። እያስተማርኳቸው መንፈቀ ሌሊት ሲሆን ሒዱ በማለት አሰናብታቸዋለሁ። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ ምእመናን ሆይ የተቀደሰ ሰማያዊ አክሊልንና መንግሥቱን ለማግኘት ስለእርሱ እንጋደልና እንሞት ዘንድ ሁላችሁም ኑ በማለት እጠራቸዋለሁ። የሚደርስባቸውን ጽኑ መከራ እያወቁ ለተጋድሎ ይሰበሰባሉ አለው።

ወገኔንና አባቴን ማን እንደሆነ ለማወቅ ከፈለግህ የአባቴ ስም ሜኖፊሎስ፣ የእናቴ ስምም ዚኖቢያ፣ የወንድሜ ስምም ኔዎን ይባላል። እርሱም አናጉንስጢስነት ተሹሟል፤ ክርስቶስንም አመስግኗል፤ እርሱም ከእኛ ጋር ስላለ የወደድከውን ማድረግ ትችላለህ። አንተ በአጋንንት የምትመራ ነህ ባለው ጊዜ ገዢው አንተ ሽማግሌ ነህና አከብርሃለሁ፤ እናትህ ታላቅና ባልቴት ናትና አፍራለሁ አለው። መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ዚኖቢስና ዚኖቢያም ለዘለዓለም ትጠፋለህና ስላንተ እናዝናለን አሉት።

ገዢውም ፈጽሞ ተቆጣ፤ ልብሷን አውልቁና በራስ ፀጉሯ ስቀሏት፤ የእርሱንም ልብሱን አውልቁና ራቁቱን ስቀሉት፤ የሚነገራቸውን እሺ ብለው አይቀበሉምና አለ። በብትር ይመቷቸው ዘንድም አዘዘ።

ወታደሮቹ ሲደበድቧቸው ቅዱሳኑ ምንም አልተናገሩም። ዚኖቢስና ዚኖቢያም እንዲህ እያሉ ጸለዩ። ዚኖቢያ ለሁሉም ክብርን የምታጎናጽፋቸው የሰማይና የምድር አምላክ ሆይ እኔንም አልብሰኝ ባለች ጊዜ ሰፊ የሆነ ወርቀ ዘቦ ልብስ ተጎናጽፋለች። ራሷንም እንደንግሥት ተሸለመች። የዚኖቢስ ልብስም ነጭ ነበር። ገዢውም እንደ አገልጋይ ወንበር ተሸክሞ ከዚኖቢስ ኋላ ይከተል ነበር። ሕዝቡን በተመለከተ ጊዜም ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ አበራልን፤ የእርሱን ስምም ወደማወቅ መለሰን እያለ ጮኸ።

ገዢው ወደ ዙፋኑ በተመለሰ ጊዜ ፈጽሞ ተቈጣ። እነዚህን ምን ታደርጋቸዋለህ የክርስቲያኖች አምላካቸው ብርቱ ነውና። ዚኖቢስና ዘኖብያም በአማልክትህ ምክንያት እንዴት ትስታለህ? ዓለምንና የሚክዱትን ሁሉ ማጥፋት የሚቻለው እግዚአብሔርን ክደኸዋል አሉት። ለየብቻቸው ትሰቅሏቸው ዘንድ ሁለት መስቀሎችን አዘጋጁ። አንዱ አንዱን እንዲያየውም እስከ ሁለት ሰዓት ተያዩ፤ እንደሚተያዩ አድርገውም ሰቀሏቸው፤ ከሰማይም ደመና መጣና ጋረዳቸው። ሰማያዊ ምግብም ሰጣቸው።

በነጋታውም አገረ ገዢው በመጣ ጊዜ ሕዝቡን ሰብስበው የእግዚብሔርን ቃል እያስተማሩ አገኛቸው። የሚሰሟቸውና አምነው የሚድኑትም ብዙዎች ነበሩ። ያላመኑትም ለዘለዓለሙ ጠፉ፤ እነዚህን ሰዎች ምን ላድርጋቸው፤ እነሆ ታላላቅ ተአምራትን ያደርጋሉና አለ። ዚኖቢስም አጋንንት እንዴት እንደሚያስቱህ አስተውል አለው። ገዢውም እንዴት እንደሚያሳስቱኝ ንገሩኝ አላቸው።

ዚኖቢስና ዚኖቢያም ኃያልና ጽኑ የምትሆን እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ጸጋዕን በሰዎች የምታሳድር፤ ውኃውን ለውጠህ ወይን የምታደርገው አንተ ነህ። ሰውንም ወደ ሃይማኖት ትመልሳለህ። አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ርኵስና ክፉ መንፈስን አስወግደው። ለሰው ልጆችም አንተ ብቻ እንደሆንህ ከአንተ ብቻ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ግለጥ አሉ።

ዚኖቢስና ዚኖቢያ ሲጸለዩ መንፈስ ርኵስ ያደረበት ሁለት ገጽ ያለው ሰው ነበር። ከአፉ ውስጥ እሳት ይወጣ ነበር፤ ከዚህ በኋላ ርኵስ መንፈስ ከሰውየው ተወገደ ሰውየውም ጤነኛ ሆነ። በዚህ ጊዜ ገዢውም ጮኸ። አጋንንት እንደሚያስቱኝ አሁን

አወቅሁ አለ:: አሕዛብም በአንድነት የክርስቲያኖች አምላክ ታላቅ እንደሆነ እናምናለን፤ የሚያምኑበትም ሁሉ እንደሚድኑ እናምናለን እያሉ በአንድ ድምፅ ጮኹ:: በዚህ ጊዜ ገዢው ተቆጣ:: ሁለት የብረት ወንበሮችን እና ሁለት የብረት ጦሮችን አምጡ፤ አስራችሁም ከእሳት ጨምሯቸው:: ስትመቷቸውም ለአማልክት መሥዋዕት አቅርቡ በሏቸው:: የአደሮ ማርና ዘይት አፍልታችሁ በእነርሱ ላይ ጨምሩት አላቸው::

ዚኖቢስና ዚኖቢያም እግዚአብሔር ኃያል አምላክ ነው አሉ:: ቅዱስ አምላካችን ሆይ ጠብቀን፤ ይቅርም በለን፤ በቅዱስ መንፈስህም ስቃዩን ሁሉ ከእኛ አስወግድ አሉ:: ቅዱሳኑ ሲጸልዩ የብረቱ ጦር በቅዱሳኑ ላይ ጉዳት ማድረስ የማይችል ሆነ:: ቅዱሳኑም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ፊታቸውን አማትበው ተቀመጡ፤ እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እየዞሩ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምሩ ጀመር:: አሕዛብም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ነው:: ዛሬ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የሚያመልኩትን ዚኖቢስንና ዚኖቢያን ከመከራ ያዳነውን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እናመሰግነዋለን አሉ::

ዚኖቢስም ሕዝቡን ለአምላካችን እንጋደል ዘንድ ያመናችሁ ሁላችሁ ወደ እኔ ኑ፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በማመንም ሰማያዊውን አክሊል እናገኝ ዘንድ እንጋደል በማለት ጠራቸው:: በቅዱሳኑ ላይ እግዚአብሔር ያደረገውን ተአምር የተመለከቱ ሁሉ እየሮጡ ወደ ዘኖቢስ ሔዱ:: በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስም ያመኑት ዳኑ:: ገዢው ግን በአየው ተአምር አምኖ ከመመለስ ይልቅ በክፋቱ እየጸና ሔደ:: እሳት አንድዱ ብሎ ዐሥር ክንድ ያህል ከፍ ሲል በዚያ እንዲጣሉ አደረገ::

ዚኖቢስና ዚኖቢያም ዘመናትን የምታፈራርቅ አንተ ነህ:: ለሰው ልጆች ተአምርህን ግለጥ፤ የዚህን እሳት ነበልባል አቀዝቅዘው፤ ገዢውንም በአንተ እንዲያምን አድርገው በማለት ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ:: ዚኖቢስና ዚኖቢያም ሲጸልዩ እሳቱ እንደ ውሃ ቀዘቀዘ:: አገረ ገዢው ውኃን የመላ ማሰሮ ይዞ የመታጠቢያውን ቤት ይጠብቅ ነበር:: እሳቱ በመቀዝቀዙ ዚኖቢስና ዚኖቢያ እግአብሔርን ፈጽመው ያመሰግኑት ጀመር:: በቅዱሳን አድሮ ተአምራትን የሚያደርግ እግዚአብሔር ቡሩክ ነው አሉ:: ገዢውም ወደ ቤቱ ሔደ፤ በዚያም ሁለት መልክ ያለው ሰው አገኘ:: ሰውዬውም ርኵስ መንፈስ ያደረበት ነበር:: ገዢውም በአንተ ምክንያት በመሳት እንጠፋለን አለው::

ከዚህም በኋላ ገዢው ዳግመኛ ከዙፋኑ ተቀመጠ:: እነዚህን ጎስቋሎች አምጧቸው አለ:: ወታደሮቹም በፍርድ አደባባይህ አሉ አሉት:: በዐደባባዩ የነበሩት ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይሉ ታላቅ ነው እያሉ ጮሁ:: ገዢውም ለታላቁ አምላክ ለባኪና ለዲዮንስዮስ መሥዋዕት አቅርቡ አለ:: ዚኖቢስም ጣኦታቱ መግደልና ማዳን እንደማይችሉ አታውቅምን አለው:: ዚኖቢስና ዚኖቢያም በጸለዩ ጊዜ መሬት ተከፍታ ሁለቱን ጣኦቶች አሰጠመቻቸው:: ቦታውም ምድረ በዳ ሆነ:: ዚኖቢስና ዚኖቢያም ገዢውን አማልክቶችህ የት አሉ በማለት አሰምተው ተናገሩ:: እርሱ ብቻ አምላክ የሆነውን እግዚአብሔርን ክደህ ጣኦታትን ብታመልክም እነርሱ ስለጠፉ ከእንግዲህ በማን ታመልካለህ? አሉት::

የተሰበሰበው ሕዝብም የክርስቲያኖች አምላክ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ተረድተናል በማለት አሰምተው ተናገሩ:: አገረ ገዢው በሕዝቡ ድርጊት በጣም ተናድዶ ወስዳችሁ ግደሏቸው በማለት አዘዘ:: በእሳት አቃጥላቸው ዘንድም በድናቸውን ጠብቁ በማለት ወታደሮችን ነገራቸው:: ወታደሮችም በክርስቶስ ያመኑትን ገደሏቸው፤ በሚገድሏቸው ጊዜም ነጎድጓድና መብረቅ ብልጭታም ሆነ:: በመደንገጥም አምስት መቶ ሴቶች እና ወንዶች ሞቱ:: ሲመሽም ከምእመናን ወገን በሌሊት ሔደው የክርስቲያኖችን በድን ወሰዱ:: ሁለት መቃብር ቆፍረው ዘኖቢያን እና ዘኖቢስን ከተሰቀሉበት አውርደው ጎን ለጎን ቀበሯቸው:: ተጋድሏቸውም በኤጌዎን አገር ሉቅያኖስ ገዥ ሆኖ ሳለ፤ በቀላውዴዎስ ዘመን ተፈጸመ:: በማግስቱም ገዢው በዐደባባይ ተቀመጠ:: በእሳት እናቃጥላቸው ዘንድ የእነዚያን ሰዎች በድን አምጡ በማለት አዘዘ::

ወታደሮችም ምሽት በሆነ ጊዜ ብልጭልጭታ፣ መብረቅና ነጎድጓድ ሆነ:: ብዙ ዝናም ዘነመ:: ዳግመኛም መንፈቀ ሌሊት በሆነ ጊዜ እንደ መብረቅ ያለ ነገር ተመለከትን:: በቤታችንም ሆነን ድምፁን ሰማን አሉት:: አገረ ገዢውም ወታደሮቹ የነገሩትን ተአምር በሰማ ጊዜ እኔም ክርስቲያን መሆን እፈልጋለሁ በማለት ተናገረ:: ገዢው እና ወታደሮችም በክርስቶስ አመኑ:: የቅዱሳኑ በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን!! ⌖

(ምንጭ:- ገድለ ሰማዕታት ቅጽ ፩)

"በመስቀሉ አርኃወ ገነተ ወተሞዓ ኃይለ ሥልጣኑ ለሞት መስቀል ቤዛነ ፀወንነ ወኃይልነ ለእለ አመነ:- በመስቀሉ ገነትን ከፈተ፤ የሞት ሥልጣን ኃይልም ተሸነፈ፤ መስቀል ላመንን ቤዛችን፣ መጠጊያችን እና ኃይላችን ነው"::

ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ

# ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ሕመምተኞች ያላት አስተዋጽኦ

ዶ/ር እንግዳ ግርማ

የአእምሮ ጤንነት ችግር የአስተሳሰብ፣ የስሜት፣ የጠባይ እንዲሁም ሌሎች የአእምሮ ተግባራት መዛባት የሚያመጡት የጤና እክል ነው። ይህም በአንጻሩ ቀላልና ጊዜያዊ ከምንላቸው የውጥረት ስሜቶች እስከ ከባድ የአእምሮ መቃወስ የሚያካትት ነው። ምንም እንኳን ከፍተኛ የአእምሮ ሕመም ደረጃ ባይደርሱም ሌሎች የውጥረት፣ የጭንቀት፣ የእንቅልፍ ማጣት ወይም የጠባይ መቀየር በጊዜያዊነት ወይም ከፍ ባለ መጠን በተደጋጋሚ ይከሠታሉ። የአእምሮ ችግር መንስኤዎች ብዙና የተለያዩ ናቸው። ሥነ ሕይወታዊ፣ ሥነ ልቡናዊ፣ ማኅበራዊ መንስኤዎች ብሎ መክፈል የተለመደና እስካሁን ተቀባይነት ያለው የአስተሳሰብ ማቀፍ ነው። ማኅበራዊ መንሥኤ በሚለው ውስጥ ባህላዊ እና መንፈሳዊ ሁኔታዎችም ይካተታሉ።

የአእምሮ ሕመም ሲባል ራሱን የጣለ፣ የተዳደፈ፣ ቆሻሻ የሚለቅም ሰው ማሰብ የተለመደ ነው። በርግጥ እጅግ በጣም ጥቂቱ የአእምሮ ሕሙማን ብቻ እንዲያ ያለውን የአእምሮ መቃወስ ምልክቶች ያሳያሉ። የሚበዙት ሕመሞች ምክንያት አልባ ጭንቀት፣ ድባቴ፣ እንቅልፍ ማጣት ወይም ከአእምሮ ዕድገት ጋር የተገናኙ ችግሮች ናቸው። በዐይን አይቶ ለመለየት አይቻልም። ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ ዘመናዊ የንግግር ወይም የመድኀኒት ሕክምና ያላቸው ቢሆንም አብዛኛው የማኅበረሰባችን ክፍል ወደ ጤና ተደራሽ አይደለም። በአገራችን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ሰዎች በቂ ሕክምና ማግኘት ባለመቻላቸው አብዛኛውን የሕይወታቸውን ዘመናት በመታሰር፣ ተስፋ በመቁረጥና በመደብደብ እንዲሁም በብቸኝነት ያለሥራ ያሳልፏቸዋል። የቤተሰብ ኑሮና ብዙ የሀገር ንዋይ እንዲሁ እንደባከነ ያልፋል።

## ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ሕሙማን የምታበረክተው አስተዋጽኦ

### ሀ. የአእምሮ ጤንነትን በመጠበቅ

ስላለን የተደከመበት የማይመስለን የአእምሮ ደኅንነታችንን

አስቀድመን እንደተመለከትነው ከሥነ ሕይወታዊ መሠረቶች ባሻገር ያሉ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ውቅሮች በብዙ ድካም የተዋቀሩ ናቸው። ለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ድርሻ ተወጥታለች። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ ምእመን በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ፣ በምግባር ላይ ትሩፋት ጨምሮ አምላኩን ለመምሰል በጎ ዘር የተዘራበት እንደሆነ በማስተማር ወደ በጎነት፣ መልካምነት፣ ቅንነት፣ ቅድስና፣ ንጽሕና እንዲያድጉ ከልጅነት ጀምሮ ዕለት ዕለት ታስተምራች። ይህም ልጆቿ በጎ ሕሊና እና አዎንታዊ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ትምክህታቸው በሆነው ከሃሌ ኵሉ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ እንደሚችሉ የሚያምኑ እንዲሆኑ አድርጎቸዋል። እንዲህ ያለው አዎንታዊ አስተሳሰብና ማድረግ እችላለሁ የሚለው እምነት ምእመናንን ከጭንቀት፣ ከውጥረትና ተስፋ ከመቁረጥ በብዙ መልኩ ይጠብቃል። ከዚህም ባሻገር ኦርቶዶክሳውያን በየማኅበረሰባቸው በእድር እንዲሳተፉ፣ ራሳቸውን ሳይኮፍሱም፣ ሳያሳንሱም ከሌሎች ጋር በሰላም እንዲኖሩ ሆነዋል።

በጎ አስተሳሰብና አምላኩን መጠጊያ ያደረገ "ሁሉን ማድረግ እችላለሁ" የሚለው እምነት ምእመናን ድሃ ቢሆኑ ሀብታም፣ ሊቅ ቢሆኑ ያልተማሩ፣ ከሰሜን ቢሆኑ ከደቡብ፣ ከምሥራቅ ቢሆኑ ከምዕራብ ያለምንም ፍርሃትና የበታችነት ስሜት በእኩል መንፈስ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረን ሁሉን በማክበር በኅብረት እንዲያመሰግኑ፣ በአንድ ሰንበቴ ማኅበር አንድ ጽዋ እንዲጠጡ አድርጓል። እንዲህ ያለው ኅብረት በደስታና በኀዘን፣ በድሎትና በእጦት በማንኛውም የኑሮ ውጣ ውረድ ሥነ-ልቡናዊና ማኅበራዊ ድጋፍ የሚገኝበት ሁነኛ መንገድ በመሆን ያገለግላል።

መኖር ሰለቸኝ፣ ራሴን አጥፍቼ አርፋለሁ፣ ለምን እኖራለሁ እና የመሳሰሉት የሚያስቆዝሙ አሳቦች በተለያዩ የአእምሮ ሕመሞች ምክንያት ወይም የሕይወትን ትርጉም በማጣት ይመጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰውን ልጅ የምድር ኑሮ ትርጉም ማስተማሯ ምእመናን የሕይወት ትርጉም እንዳይጠፋቸውና በቀቢጸ ተስፋ እንዳይኖሩ ትልቅ መሠረት ሆኗል። ከዚህም በላይ የኦርቶዶክሳውያን ልጆች የሰብእና አወቃቀር ዋነኛ ማንጸሪያ ፈጣሪያቸውና አምላካቸው ስለሆነ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴዎቻቸው "ይህን እግዚአብሔር ይወደዋል?" በማለት ራሳቸውን እንዲጠይቁ እና ከክፋትና ጥፋት እንዲጠበቁ ሆነዋል። ሌሎች ላይ ቅያሜ ከመፍጠር፣ ጫና ከማድረግ፣ ከመጉዳት ተጠብቀዋል።

ሌላው ትልቁ የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ምሥጢረ ንስሓ ነው። ምእመናን ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው ባሻገር ስለጭንቀታቸው፣ የዕለት ተዕለት ተግዳሮቶቻቸው፣ ማኅበራዊ ውጣ ውረዶቻቸው፣ የቤተሰብ ሕይወታቸው ከመምህረ ንስሓቸው ጋር ይወያያሉ። እነዚህን ሁሉ የሚያዳምጥ ጆሮ ማግኘት በራሱ ትልቅ ዕረፍት

የሚሰጥ ነው፡፡ ለየተግዳሮቶቻቸው ጊዜ ሰጥቶ መመካከርና የመፍትሔ አሳብ ማምጣት መቻል ደግሞ ትልቅ መንፈሳዊ ሕክምና ነው፡፡ ጭንቀት፣ ውጥረትና ሌሎች የአእምሮ ጫናዎችና ሕመሞች በዚህ መልክ ሲታከሙ ኖረዋል፡፡

ሰዎች ኀዘን በደረሰባቸው ጊዜ የሚጽናኑባት እጅግ ጠቃሚ ሥርዓት ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ኀዘን ጊዜ የሚወስድ እንደመሆኑ በየደረጃውና በየጊዜው በካህናትና በምእመናን የማጽናናት ሥራ ትሠራለች፡፡ በዚህም ሰዎች ከኀዘን ጋር የተገናኘ የአእምሮ ጭንቀትም ሆነ ሌላ ሕመም እንዳይከሠትባቸው ስትረዳ ቆይታች፡፡ ድንገተኛ አደጋ/ጥቃት የደረሰባቸውን በቃለ እግዚአብሔር ማጽናናት፣ ከተቻለ ቁሳዊ ድጋፍ ማድረግ እና ምእመናን ላዘኑና ለተጎዱ ወገኖች እንዲደርሱ ማበረታታት የቤተ ክርስቲያን የዘመናት ተግባር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ሰዎች ከአሰቃቂ ክሥተት በኋላ ከፍተኛ የአእምሮ ውጥረት እንዳይከሠትባቸው እንዲህ ያለው ማኅበራዊና መንፈሳዊ አገልግሎት ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ በሰሞኑም ደጋግመን እያየን ያለነው ይህንኑ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን የዘመናት ገጽታ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ደኅንነት የምታበረክተው አስተዋጽኦ በአደጋ፣ በሕመምና በጭንቀት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመልካሙም ጊዜ ጭምር ነው፡፡ እንዲህ ላለው የቤተ ክርስቲያን አበርክቶ ሰ/ት/ቤቶች ጥሩ ምስክሮች ይሆናሉ፡፡ የኦርቶዶክሳውያን ልጆች በሥነ ምግባር እንዲታነጹ፣ ሀገራቸውን እንዲወዱ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ ለወላጆቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ በሰ/ት/ቤት ተኮትኩተው ያድጋሉ፡፡ ወጣቶች ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ፣ ከሱስ ተጠብቀው፣ እርስ በእርስ እየተዋደዱ እንዲኖሩ በማድረግ ሰ/ት/ቤቶች የፈጠሩት ትልቅ የአዳጊዎችና ወጣቶች ኅብረት ብዙ ትውልድ የሚታደግ አገር ያወቀው፣ ፀሐይ የሞቀው ሐቅ ነው፡፡

በመምህረ ንስሓ በኩል ከወላጆች፣ በሰንበት ት/ቤት በኩል ከአዳጊዎችና ወጣቶች፣ በስብከተ ወንጌል በኩል ከመላ ቤተሰቡ በመድረስ ሰላማዊ የክርስቲያን ቤተሰብ እንዲኖራቸው፣ ወላጆች ለልጆች ፍቅርና ክብካቤ እንዲሰጡ፣ ልጆች በሥነ ምግባር ታንጸው፣ ወላጆቻቸውን አክብረው እንዲያድጉ በማድረግ ወላጆቻችን ከጭንቀትና ከውጥረት፣ ልጆቻችን ከአስተዳደግ ጋር ተያይዘው ከሚመጡ ብዙ የአእምሮ ጤና እክሎች መታደግ ወይም መቀነስ ሌላው የቤተ ክርስቲያን የሚታይ አስተዋጽኦ ነው፡፡

በሥነ ልቡና ዓለም ብዙ ካጨቃጨቁ ጉዳዮች መካከል አንዱ ሃይማኖተኝነት (መንፈሳዊነት) ነው፡፡ በዘመናዊ የሥነ ልቡና እና የአእምሮ ሕክምና ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ እየተጠኑ ካሉ ርእሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ መንፈሳዊነት/ ሃይማኖተኝነትና አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነት ያላቸው ውስብስብ ግንኙነት ነው፡፡ አሁን ባለው መረጃ መሠረት መንፈሳዊነት ለአማኞች ከፍተኛ የአእምሮ ሰላም ይሰጣል፡፡ ለአካላዊ ሕመም የመጋለጥ እድልን ይቀንሳል፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆችዋ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በርትተው እንዲኖሩ ማስተማር ዛሬ ሳይንስ ጠቃሚ ነው ብሎ ስለተናገረ ሳይሆን በዘመናት ሁሉ የአገልግሎቷ ማጠንጠኛ አድርጋ ስትፈጽመው የኖረችው ዋነኛ አገልግሎቷ ነው፡፡ መንፈሳዊነት ከሰማያዊ ጥቅሙ ሌላ እንደ ዳረጎት አእምሯቸውና አካላቸው የተረጋጋ፣ ለሕመም ተጋላጭነታቸው የቀነሰ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## ለ. በማከም/በፈውስ

ቤተ ክርስቲያን የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ያሉ ምእመናን ዕረፍት የሚያገኙባት ባለ መድኃኒት እንደሆነች እሙን ነው፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ የአእምሮ ሕመም ያለባቸውን ሰዎች ብናይ በሥርዓተ ጸሎቱ፣ በስብከቱ፣ በመዝሙሩ የመንፈስ ዕረፍት፣ የአእምሮ መረጋጋት ያገኛሉ፡፡ ይህንንም እንደ የቡድን ሕክምና ልናየው እንችላለን፡፡ ከዚህም በላይ ምእመናን በንስሓ አባቶች በኩል የየግል ጭንቀቶቻቸውን እንዲወያዩ እና እንዲፈቱ ታደርጋለች፡፡ የቤተ ክርስቲያን ምክር ተስፋ በመቁረጥ፣ በከፍተኛ ኀዘን፣ በቤተሰብ አለመረጋጋት ውስጥ ለሚገኙት የጭንቀታቸው ማቃለያ፣ የችግራቸው መፍቻ መንገድም ሆኖ ያገለግላል፡፡

በኢትዮጵያ ከፍተኛ የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ሕሙማን የሚበዙት ወደ ጸበል ቦታዎች ይሔዳሉ፡፡ ቍጥራቸው በዘመናዊ የሕክምና ተቋማት ከሚገኙት በብዙ እጥፍ ይበልጣሉ፡፡ ሁሉም ወደ ሐኪም ቤት ቢመጡ ያለው የአእምሮ ሕክምና ተቋም ከሚቋቋመው እጅግ የበዛ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የአእምሮ ሕሙማን የሆኑ ጸበልተኞችን አቅፋ በመያዝ ምግበ ነፍስ እየመገበች ታኖራቸዋለች፡፡ የሱስ ሕመም ያለባቸውን ወጣቶች በቅጽሯ ቆይተው፣ መንፈሳቸውን አድሰውና አገግመው እንዲወጡ ትሠራለች፡፡ ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰባቸው የሚጠቅሙ እንዲሆኑ ታዘጋጃቸዋለች፡፡ እንዲህ ያለው ጉልህ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ከሕሙማኑ ባሻገር ወላጆች እና ቤተሰቦች ከፍተኛ ዕረፍትና የመንፈስ እድሳት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው በሳይንስ ከምንረዳው በላይ ከሆነው የፈውስ አገልግሎቷ ባሻገር በቤተ ክርስቲያን እየተከናወነ ያለውን የሚመለከት ነው፡፡

ስንዱ እመቤት የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን በኢትዮጵያ ለአእምሮ ጤና ያበረከተችው ተቈጥሮ የሚያልቅ፣ ቃላት አሳክተው የማይገልጡት ነው፡፡ መዋቅሯም ይህን ለማድረግ የተመቸ ነው፡፡ ከዚህ የበለጠ ለማድረግ የተለየ አወቃቀር አይጠይቅም፡፡ ምእመናን ላይ መሥራትና በሁሉም ዘርፍ ዘመኑን መዋጀት ይገባል፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን የሚከተሉትን ተግባራት አጠናክራ ብትቀጥል መልካም ነው፡፡

## ሀ. ምእመናንን ማስተማር

ማንኛውም ዓይነት ሕመም ልንታመም እንደምንችለው ሁሉ አእምሯችንንም ሊያመን ይችላል፡፡ የአእምሮ ጤና

መቃወስ በተለየ መልኩ የደካማነት ወይም የኃጢአት ምልክት አይደለም፡፡ስለዚህ ምእመናን ማንኛውም አካላዊ ሕመምን በሚያዩበት የአእምሮ ሕመምንም እንዲረዱት ማድረግ የሕሙማን መገለልና ስቃይ ይቀንሳል፡፡ ወደ ሕክምና ቦታ ወይም ቤተ ክርስቲያን የመምጣት ዕድላቸውን ይጨምራል፡፡ ይህን ውጤት ለማምጣት ስለሕመምና ደዌ በተነሣበት አጋጣሚ ሁሉ ስለ አእምሮ ሕመም ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ስፍራዎች የተጠቀሱትን የአእምሮ ሕሙማን የምሕረት ባለቤት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ሳይጸየፍ አቅርቦ እንዳዳናቸው እየጠቀሱ ማስተማር ምእመናን በሽተኞችን እንዳያገሏቸው ግንዛቤ ለመፍጠር ይረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁሉን ማዳን የሚችለው አምላካችን በልዩ ልዩ መንገዶች እንደሚፈውስ፣ ዘመናዊው ሕክምናም የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ፣ ምእመናን እየተጠመቁ መድኃኒት መውሰድ እንደሚችሉ፤ መድኃኒት እየወሰዱ ባሉበት ጊዜም አስቀድመው መጠመቅና ከተጠመቁ በኋላ መድኃኒቱን መውሰድ እንደማይከለከሉ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ወይ በመድኃኒት አልያም በጸበል ከሚል አማራጭ፣ ፉክክርና ድርቅና ወጥተው፣ እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መንገድ እንደሚፈውስ ተረድተው ሁለቱንም እንዲጠቀሙ ማበረታታት ይገባል፡፡

## ለ. ምሥጢረ ንስሓ

ንስሓ ለድኅነት የተሰጠን የቸርነት በር ነው፡፡ እጅግ ብዙ ምእመናን በዚህ የምሥጢር በር እየገቡ ከአምላካቸው ጋር የለያቸውን ነገር በማስወገድ ኅብረታቸውን ይመልሳሉ፡፡ ይህን ለምእመናን መንፈሳዊም ሆነ ምድራዊ ሕይወት ወሳኝ የሆነ ምሥጢር የሚያስገኘውን ጥቅም ምእመናን እንዲረዱት ከማድረግ በተጨማሪ የምእመናንን የንስሓ ሕይወት የሚከታተል ክፍል ማቋቋም፣ ምእመናን በንስሓ ሕይወት እንዲጠቀሙ ማበረታታት ቀዳሚ ተግባራት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ካህናት አባቶች ከተነሳሕያን ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት፣ በሚያናግሩበት ጊዜ ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች፣ ስለሚወያዩባቸው ዋነኛ ፍሬ አሳቦች የሚያተት የሥልጠና መመሪያ ማዘጋጀት እና ማሠልጠን፡፡ ከመንፈሳዊው ጥበብ በተጨማሪ በዘመናዊው የንግግር ሕክምና በጥናት የተረጋገጡ መንገዶችን መጠቀም የሚችሉ ብዙ ካህናትን ማፍራት ያስፈልጋል፡፡ ይህም በቀቢጸ ተስፋ ያሉ ወንድሞችና እኅቶችን የበለጠ ለመርዳት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡

## ሐ. የሱስ ማገገሚያ ሥርዓት መዘርጋት

ወጣቶች በየጸበል ቦታው የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ምግብ እየተመገቡ "አምጣ አምጣ" የሚላቸውን የሱስ ስሜት ተቋቁመው ይቆያሉ፡፡ ሥርዓት ተደንግጎለት በሱስ ለተጎዱ ጸበልተኞች በተለየ መልኩ ድጋፍ የሚደረግ ቢሆን እጅግ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡ በልዩ ልዩ ሱስ የተጠመዱ ወንድሞችን እና እኅቶችን መንፈስ የሚያንጽ፣ የተጠና እና በየደብሩ/ገዳሙ የተቀናጀ የስብከተ ወንጌል፣ የውይይት፣ የንግግር ሕክምና እና የመዝሙር ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ ውጤቱ የሚለካና በየጊዜው የሚሻሻል ኦርቶዶክሳዊ ወጣቶችን የመታደጊያ መንገድ እንዲሆን ይረዳል፡፡ እንዲህ ባለው መንገድ ታንጸው የወጡ ወጣቶች ከሱስ ከማገገማቸው በላይ ለቤተሰብ፣ ለአገር እና ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## መ. የጸበል ቦታዎች

ክርስቲያኖች በየአድባራቱና በየገዳማቱ ተሰባስበው በመጠመቅ ድኅነተ ሥጋ፣ ድኅነተ ነፍስ ለማግኘት ይለምናሉ፤ ይማልላሉ፡፡ ይሁን እና ጥቂት በማይባሉ ጊዜያት ይህ የሚሆነው ካላስፈላጊ ሥቃይና እንግልት ጋር ነው፡፡ ጸበልተኞቹ የአእምሮ ሕሙማን ለግርፋት እና ለሰንሰለት እስራት ይዳረጋሉ፡፡ በአስጠማቂዎች ይደበደባሉ፡፡ ብዙዎች የጸበል ስፍራዎች በቂ የውኃና የንጽሕና መጠበቂያ ቦታዎች የሏቸውም፡፡ በአንዳንዶቹ ገዳማት እና አድባራት ምእመናን ከመሐል ከተማ ባልተናነሰ የቤት ኪራይ ኑሯቸው ይናጋል፡፡ እነዚህን ችግሮች መቅረፍ የጸበል ቦታዎች ተቀዳሚ ሥራ መሆን አለበት፡፡ እግዚአብሔርን ብሎ ቤተ ክርስቲያንን ተጠግቶ ያለ ሕመምተኛ ተጨማሪ ሕመምና እንግልት ሊደርስበት አይገባም፡፡

ጸበልተኞች ከመጠመቅ፣ ከጸሎትና ከመንፈሳዊ አገልግሎት በተረፋቸው ጊዜ ቁጭ ብሎ ከማውራት፣ ዝም ብሎ ከመቆዘም ወይም ለክፉ አሳብ ማደሪያ ከመሆን እንደየአቅማቸው በሥራ እንዲያሳልፉ ማድረግ ለገዳማቱ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይገባል፡ ፡ ለአብያተ ክርስቲያናቱ ከሚኖረው በጎ ትሩፋት ባሻገር ጸበልተኞች የመዳን ሒደታቸውን እንዲያፋጥኑ፣ ወደ መደበኛ ሕይወታቸው ሲመለሱ ለሚኖራቸው የሥራ ሕይወት ዝግጅት እንዲያደርጉ ያግዛል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷ በየዘመናቱ የሚከሠቱ ችግሮችን የዋጀ እንዲሆን ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱ ለአእምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ተቋም አዘጋጅታ ተቋሙንም በሃይማኖት በጸኑ፣ በሙያው በሠለጠኑ ክርስቲያኖች እንዲመራ ማድረግ ይኖርባታል፡፡ ይህም አገልግሎቷ ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ✤

# ጸጸት

**በእንዳለ ደምስስ**

ቀኑ ለምሽት ተራውን እየለቀቀ ነው፡፡ ፀሐይ የእሳት አሎሎ መስላ ከመጥለቂያዋ ገብታ ከአድማስ ማዶ ለመሸሸግ ትጣደፋለች፡፡ አክሊሉ አራት ኪሎ ከሚገኘው መሥሪያ ቤቱ ወጥቶ በቀጥታ ያመራው ሲኤምሲ ቅዱስ ሚካኤል ጀርባ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ነው፡፡ ጠዋት ከቤት ከመውጣቱ በፊት ልጁ ናሆም የጠየቀው ጥያቄ ጤናማ ጥያቄ ነው ብሎ ማመን ቸግሮት ዕረፍት ሲነሣው ውሏል፡፡ በቂ መልስ ሊሰጠው አለመቻሉም አስጨንቆታል፡፡ የጠዋቱ ሁኔታ እየተመላለሰ ይረብሸዋል፡፡ የ፲፪ እና የ፰ ዓመት ልጆቹ ቀድመውት ከእንቅልፋቸው ተነሥተው ወደ ትምህርት ቤት ለመሔድ እየተዘጋጁ ነው፡፡ አክሊሉ ሌሊቱን ጥሩ እንቅልፍ ባለመተኛቱ ድካም ቢሰማውም እየተነጫነጨም ቢሆን ተነሣ፡፡ ቁርስ የመብላት ልምድ ስለሌለው ባለቤቱ እስከታቀርብለት አልጠበቀም፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ለመሔድ የሚጣደፉትን ልጆቹን ስሞ ወደ በሩ እያመራ ሳለ የመጀመሪያ ልጁ ናሆም ያልጠበቀው ጥያቄ ጠየቀው፡፡

"አባዬ እኛ ለምንድነው ቤተ ክርስቲያን ሔደን የምንሰግደው?" ሲል ጠየቀው፡፡ የ፲፪ ዓመት ልጅ የሆነው ናሆም መጠየቅ ይወዳል፡፡ ትምህርት ቤት ከጓደኞቹ ጋር ሲጫወት የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ከአእምሮው በላይ ስለሚሆኑበት ወደ ቤት መጥቶ አባቱን ይጠይቃል፡፡ አክሊሉ ከቢሮ ይዞት የመጣውን ሥራ ለማጠናቀቅ በሚል ትኩረቱ ሁሉ ኮምፒዩተሩ ላይ ቢሆንም ለልጁ ጥያቄ በጥቂቱም በተከፈለ ልቡ ለመመለስ ይሞክራል፡፡ ብዙ ጊዜ በልጁ ጥያቄ ይገረማል፤ የልጁ ጓደኞች ፈጣን አእምሮ ያስደንቀዋል፡፡ አንዳንዴም ያበሳጨዋል፡፡ የዛሬው ጥያቄ ጤናማ አልመሰለውም፡፡

"ማነው ይህን የጠየቀህ?" አለው ምላሹን ከመስጠት ተቆጥቦ፡፡ አጠገቤ የሚቀመጠው ጓደኛዬ ሙሴ ነዋ፡፡ ምሳ ስንበላ ዓይኑን ጨፍኖ ነው የሚጸልየው፤ እመቤታችንን ደግሞ አይወዳትም፡፡እኔም ዝም አልለውም ለምን ይሰድባታል ብዬ እንደባደባለን፡፡ ባለፈው እንኳን የአማርኛ አስተማሪያችን ቲቸር በላቸው ገረፈኝ ብዬ አልነገርኩህም?"፡፡ ለምን እንደገረፈህ እኮ አልነገርከኝም?" አለ ምክንያቱን ሳይጠይቀው ማለፉን አስታውሶ፡፡ በሥራ እየተጠመደ ልጆቹ የሚገጥማቸውን ችግር ለመፍታትም ሆነ ምን ዓይነት ተማሪዎች እንደሆኑ ለመጠየቅ ከመምህሮቻቸው ጋር ለመመካከር ጊዜ ሰጥቶ አያውቅም፡፡ ከትምህርት ቤት መልእክት ሲመጣ፣ ስብሰባ ወይም ውጤት ለመቀበል እንኳን ሔዶ አያውቅም፡፡ የልጆቹን ጉዳይ ለባለቤቱ ለሐና ሰጥቶ ልጆቹን መከታተል አለመቻሉ አሳፈረው፡፡ "ወይኔ ልጆቼ! ወልጄ ተውኳችሁ ማለት ነው?" በማለት ሁለቱን ልጆቹን እያፈራረቀ የተመለከታቸው የጥፋተኝነት ስሜት እየተሰማው ነበር፡፡

"ሌባና ፖሊስ ስንጫወት ሳሸንፈው ጊዜ እመቤታችንን ተሳድቦ ሲሮጥ ድንጋይ ወርውሬ ጭንቅላቱን መታሁትና አለቀሰ፡፡ የአማርኛ አስተማሪያችን ደግሞ ገረፈኝ፡፡ ከዚያ ደግሞ አስታረቀን" አለ ጣፋጭ በሆነ አንደበቱ፡፡ "ታዲያ ይህን ጥያቄ ሙሴ ለምን ጠየቀህ?" አለው በስጋት፡፡ "ሊያናድደኝ ነዋ፡፡ ስላልመለስኩለት ለጓደኞቻችን ተናግሮ አስቆብኛል" አለ እየተሽማቀቀ፡፡ "አየህ ልጄ እሱ የሚልህን አትስማው፡፡ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ አለ፡፡ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ስሙ የሚጠራበት፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የምንቀበልበት፣ ጸሎት የምንጸልይበትና ጸሎታችንም የሚሰማበት ቅዱስ ቦታ ስለሆነ በእግዚአብሔር በቅድስናው ስፍራ በቤተ ክርስቲያን እንሰግዳለን፡፡ ሁል ጊዜም ቤተ ክርስቲያን ሔደን እንሰግዳለን፣ እንሳለማለን" አለ፡፡ መልሱ ልጁን አርክቶት ይሁን አይሁን ለማረጋገጥ በትኩረት አስተዋለው፡፡ ግራ እንደተጋባ ሲረዳ ከአቅሙ በላይ በሆነ አገላለጽ ምላሹን እንደሰጠው ተረዳ፡፡ አቅልሎ ለመንገር ቃላት መምረጥ ፈለገ፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ጠቅሶ ሊያስረዳው አሰበ፡፡ ነገር ግን ከአቅሙ በላይ በሆነ መንገድ የባሰ እንዳያደናግረው ስለሰጋ እንዴት ላስረዳው በሚል ተጨነቀ፡፡ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ትዝ አለው፡፡ "ይኸውልህ ልጄ ሕዝቅኤል የሚባል የእግዚአብሔር የቢይ"በሰሜኑም በር መንገድ በቤቱ ፊት አገባኝ፡፡እኔም አየሁ፣ እነሆም የእግዚአብሔር ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶት ነበር፡፡ እኔም በግንባሬ ተደፋሁ" (ሕዝ.፵፬.፬) በማለት ተናግሯል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ስንሔድ ራሳችንን አዘጋጅተን መሆን አለበት፡፡ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በጎችን ሲጠብቅ በአጠገቡ የነበረ ቁጥቋጦ በእሳት ሲቃጠል ያየ መሰለው፡፡ ወደ ቁጥቋጦው ቀርቦ ሲመለከት ግን ቁጥቋጦው አልተቃጠለም ነበር፡፡ የእግዚአብሔርም መልአክ "ሙሴ ሙሴ ወደዚህ አትቅረብ፡፡ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ" (ዘፀ.፫.፬-፭) አለው፡፡መልአኩ እንዲህ ያለው ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰች መሆኗን ሲያስተምረው ነው፡፡ እኛም ቤተ ክርስቲያን ስንገባ ጫማችንን አውልቀን እንሳለማለን፣ እንሰግዳለንም፡፡ "አሁንስ ገባህ?" አለ ልጁ በመልሱ ይርካ አይርካ መገመት እያቃተው፡፡ ከአእምሮ በላይ የሆኑ ጥቅሶችን እየደረደረ ሊያስጨንቀው አልፈለገም፡፡ ሰዓቱን ሲመለከት ለልጆቹም ሆነ ለእርሱ እንደረፈደ ተረዳ፡፡

"ማታ በደንብ እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ ከማንም ጋር እንዳትጣላ" ብሎ ሁለቱንም ልጆቹን ስሞ ቅር እያለው ወጣ፡፡ አክሊሉ ለስሙ

መሥሪያ ቤቱ ይሒድ እንጂ ቀኑን ሙሉ ለልጁ እንዴት ማስረዳት እንዳለበት ቃላት እየመረጠ አንዱን እየጣለ ሌላውን እያነሣ በአሳብ ሲባዝን ውሎወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ተወልዶ ባደገበት ጎጃም በልጅነቱ ከፊደል እስከ ዳዊት በአጥቢያቸው ወንበር ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት የኔታ ቢማርም ጠለቅ ብሎ እንደ ሌሎቹ የሰፈሩ ልጆች የአብነት ትምህርት አልተማረም፡፡ አጎቱ በልጅነቱ አዲስ አበባ ወስደው ዘመናዊውን ትምህርት አስተማሩት፡፡ ዛሬ በአንድ መንግሥት መሥሪያ ቤት በኃላፊነት በመሥራት ላይ ነው፡፡ ልጆቹን ሰንበት ትምህርት ቤት አለማስገባቱ ጸጸተው፡፡ የሚያውቀውን ለልጆቹ አለማስተማሩ ቆጨው፡፡

> “ማታ በደንብ እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ ከማንም ጋር እንዳትጣላ” ብሎ ሁለቱንም ልጆቹን ስሞ ቅር እያለው ወጣ፡፡ አክሊሉ ለስሙ መሥሪያ ቤቱ ይሒድ እንጂ ቀኑን ሙሉ ለልጁ እንዴት ማስረዳት እንዳለበት ቃላት እየመረጠ አንዱን እየጣለ ሌላውን እያነሣ በአሳብ ሲባዝን ውሎ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

ገና ወደ ቤት ከመግባቱ በጉጉት ሲጠብቀው የዋለው ልጁ ዘሎ አንገቱ ላይ ተጠመጠመ፡፡ “አባዬ እ- እ- ጠ- ጠ- ዋት የ- የነገረከኝን ሁሉ ለሁሉም ጓደኞቼ ነገርኳቸው፡፡ ሙሴ መልስ መመለስ አቃተው፡፡ እንዳበሸቀኝ አናደድኩትና ጓደኞቼ ሳቁበት” አለ ናሆም በድል አድራጊነት ፈንድቆ “ጎበዝ የኔ ልጅ፡፡ መጣሁ ልብሴን ልቀይር” ብሎ ወደ መኝታ ቤት ገባ፡፡ ናሆም ለረጅም ጊዜ ለአእምሮው ጥያቄ የፈጠረበትንና መልስ ያጣለትን ተጨማሪ ጥያቄ ለአባቱ ለመጠየቅ ተዘጋጀ፡፡ ማታ ለጠየቀው ጥያቄ በሰጠው መልስ ጓደኛውን ድል ስላደረገ ተጨማሪ ማብራሪያ አልፈለገም፡፡ ለዛሬው ጥያቄ ደግሞ ተዘጋጀ፡፡ አክሊሉ ከመሥሪያ ቤት ሆኖ ሲሠራ ውሎ አላልቅ ያለውን ሥራ ከቤቱ ለመጨረስ ፍላጎት ቢኖረውም ከዚያ በፊት ልጁን ማረጋጋት እንዳለበት ስለተረዳ ልብሱን ቀይሮ ለጥቂት ደቂቃዎች ከልጆቹ ጋር ማሳለፍ እንዳለበት አምኗል፡፡ የልጆቹን ኃላፊነት በሚስቱ ላይ ጥሎ ስለነበር ኃላፊነቷን በአግባቡ ባለመወጣቷ አጉረመረመ፡፡

ሳሎን እንደተቀመጡ ናሆም ጥያቄውን ለማንሣትፈለገ፡፡ “አሁን ጠዋት ለጠየቅሽኝ ጥያቄ መልሱን ላብራራልህ” አለ አክሊሉ ሁለቱን ልጆቹን በግራ እና በቀኝ አስቀምጦ፡፡ “ገብቶኛል አልፈልግም፡፡ ሌላ ጥያቄ ደግሞ አለኝ” አለ ናሆም አባቱ ይመልስለት ዘንድ ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ፡፡ ስጋት እየገባው “ምንድነው ጥያቄህ?” አለ፡፡ “እ- እነ ሙሴ ለምንድነው ዓይኖቻቸውን ጨፍነው የሚጸልዩት? ብታይ እ- እሱ ዓይኖቹን ጨፍኖ ሲጸልይ ጓደኞቼ ምሳውን ስለሚሰርቁበት ይደባደባሉ፡፡ ጋሼ በኃይሉ ደግሞ እየሮጡ መጥተው ሁላችንንም ይገርፉናል” አለ፡፡ “አንተ ግን በእንደዚህ ዓይነት መጥፎ ድርጊት ውስጥ መሳተፍ የለብህም፡፡ መጣላት፣ ተንኮል መሥራት፣ መሳደብ ኃጢአት ነው ብዬ ከዚህ በፊት ነግሬህ የለም?” አለው፡፡ ልጁም እኔ የምጣላው በቤተ ክርስቲያን ነገር ሲሳደቡ ብቻ ነው፡፡ አሁን የጠየቅሁህን ጥያቄ አትመልስልኝም?” አለ አንገቱን ሰበር አድርጎ መሬት መሬት እያየ፡፡ “እመልስልሃለሁ፡፡ ዓይንን ጨፍኖ መጸለይ ትክክል አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የብርሃን እንጂ የጨለማ አምላክ አይደለም፡፡ ጨለማ የሰይጣን ምሳሌ ነው” አለ እንዴት ማስረዳት እንዳለበት እያሰላሰለ፡፡ ወዲያው ባለቤቱ ሥራ ውላ “እንዴት ዋላችሁ?” ብላ ሦስቱንም ስማ ወደ ውስጥ ገባች፡፡

“እንዴ አባዬ ጨለማንና ብርሃንን፣ ሁሉንም ነገር የፈጠረው እግዚአብሔር ነው ብለህ አልነገርከኝም? እንዴት እግዚአብሔር የብርሃን አምላክ ብቻ ይሆናል?” ናሆም ሌላ ጥያቄ አባቱ ላይ ጫነ፡፡ አክሊሉ በልጁ ፈጣን ጥያቄ ተደናገጠ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደማደጉ ዘመናዊውን ትምህርት ብቻ ሲያሳድድ ለመንፈሳዊው ዕውቀት ባዕድ እየሆነ መምጣቱን እነዚህን ቀላል የሚመስሉ ጥያቄዎችን መመለስ ባለመቻሉ በራሱ አዘነ፡፡ መልሶ ደግሞ የሚያውቀውን ለማስረዳት ለልጁ ከአቅሙ በላይ እንደሚሆንበት ተረዳ፡፡ “አየሽው ልጅሽ የሚጠይቀው ጥያቄ? በደንብ ብትከታተይው ኖሮ እንዲህ ጠያቂ ብቻ አይሆንም ነበር” አለ አክሊሉ ሐና ከመኝታ ቤት ወደ ሳሎን ስትወጣ፡፡ ደካማ ጎኑን በሚስቱ ለማሳበብ እየሞከረ፡፡

"ምነው ገና ከመግባቴ ነገር ይዘህ ቆየኸኝ። ልጆቹ እንደሆነ የእኔም የአንተም ናቸው። ያለን ኃላፊነት እኩል ነው። ከቢሮ እያመሸህ ትመጣለህ። ቤት መጥተህ ለቤተሰብህ ጊዜ መስጠት ሲገባህ ሥራ ይዘህ ከኮምፒዩተርህ ጋር ትፋጠጣለህ። እኔ ብቻዬን ምን አድርጊ ነው የምትለኝ?" በማለት እጆቿን ወገቧ ላይ አድርጋ በንዴት ተናገረችው። "የልጆቹን ኃላፊነት የወሰድሽው አንቺ ነሽ። ምን በሉ፣ ምን ለበሱ ብቻ ሳይሆን ውሎአቸውንም መከታተል አለብሽ። እኔ ጊዜ እንደሌለኝ ታውቂያለሽ" አለ ሚስቱን እንዳስቆጣት ሲረዳ ንግግሩን በማለዘብ። "እኔም እኮ መሥሪያ ቤት ስለፋ ውዬ ነው የምመጣው። ቤት መጥቼ ደግሞ የቤት ውስጥ ሥራው ይጠብቀኛል። አንተ እንደሆንክ የወደቀ ዕቃ እንኳን አታነሣም። ውለህ፣ አምሽተህ፣ እንደገና ኮምፒዩተር ላይ ታፈጣለህ። ጊዜ ወስደህ የቤት ሥራቸውን እንኳን ለመከታተል አትሞክርም። እኔ ለስንቱ ልሁን?" በማለት ሶፋ ላይ ስትቀመጥ ልታለቅስ ደርሳ ነበር። በሁኔታዋ አባትና ልጆች ተደናገጡ። ልጆቹ ሮጠው እናታቸው ላይ ተጠመጠሙ። የእናቷን ማልቀስ የተረዳችው ኤፍራታ እናቷን እንዳቀፈች አለቀሰች። አክሊሉ የሚይዘውን፣ የሚጨብጠውን አጣ። የተፈጠረውን ችግር ለማስወገድ ቢቸግረውም ለቅሷቸውን እስኪያቆሙ ጠብቆ "ይቅርታ እናቴ ሳላስበው አስቀየምኩሽ" ብሎ ሐናን ለማባበል ሞከረ።

"ለምን ታስቃየኛለህ? ሁሉን ችዬ ዝም ስላልኩህ ነው? ለምን አታግዘኝም? የቢሮ ሥራህን ቢሮ ውስጥ ጨርሰህ ወደ ቤትህ መምጣት፣ ባትጨርስ እንኳን በማግስቱ ትደርስበታለህ፣ ቤት ውስጥ ደግሞ ለቤተሰብህ ጊዜ ስጥ። ሁሉን ነገር እኔ ላይ ጥለህ እንዴት እችላለሁ? አላሳዝንህም? ለልጆችህስ አታዝንምን?" አክሊሉ የልጁን ብቻ ሳይሆን የባለቤቱን ያልተመለሱ ጥያቄዎች መመለስ ተሳነው። ምን ያህል ቤተሰቡን እንደበደለ ሲያስበው ለጸጸት እጁን ሰጠ። ችግር ያመጣል ብሎ ያላሰበው ጉዳይ ቤተሰቡን መጉዳት መቻሉ አሳፈረው፤ ቀና ብሎ ባለቤቱንና ልጆቹን ለማየት አቅም አጣ። ሳሎኑ በዝምታ ተዋጠ። ሁሉም ዝም . . . ። የቤቱ ራስ የሆነው አክሊሉ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት መሥዋዕትነት መክፈል እንዳለበት ተረዳ። ጭቅጭቁ በዚሁ ከቀጠለ አቅጣጫው እንደሚቀየር ገብቶታል። "ይቅርታ የኔ ውድ! እውነትም በድያለሁ። ነገር ግን ይህን ያህል እስክትጎጂ ለምን ጠበቅሽ? እስከ ዛሬ ለምን አልነገርሽኝም?" አለ ባለቤቱን ቀና ብሎ ለማየት እየተሽማቀቀ።

ልጆቹ በየተራ አንድ ጊዜ አባታቸውን፣ መልሰው ደግሞ እናታቸውን እያዩ ዓይኖቻቸውን ያቁለጨልጫሉ። ላስተዋላቸው ፊታቸው ላይ ፍርሃት ይነበባል። "እንዴት አይገባህም? እኔ ስንት ቦታ ልበጣጠስ?" አለች በቁጣ። "ይቅርታ አልኩሽ እኮ። አሁንም ቢሆን አልረፈደምና የተፈጠረውን ችግር በጋራ እንፍታው። ተጨቃጭቀን አንዘልቀውም። ቤታችንን ለማፍረስ የሚታገለንን ዲያብሎስ ማሳፈር አለብን። እኔ እኮ የተሻለ ኑሮ እንኖራለን ብዬ ነው ያለ ዕረፍት የምሠራው እንጂ ቤተሰቤን ለመጉዳት አይደለም። ከእንግዲህ ስለነገ እያሰብኩ ዛሬን አላበላሽም። እየኖርን ያለነው ዛሬን ነው። ነገ ምን እንደሚፈጠር አናውቅም። ለምን ራስህንም ቤተሰቦችህንም ትጎዳለህ? ትዳራችን በሚመጣ ገንዘብ ብቻ አይቆምም። ስንተሳሰብ፣ ስንረዳዳ፣ አንዳችን ለአንዳችን ስንጨነቅ ነው። በውድቅት ሌሊት ትተኛለህ፤ ጎሕ ሲቀድ ትወጣለህ። እሑድ እንኳን ቅዳሴ አለቀ አላለቀ እያልክ በመቁነጠነጥ ትጨርሳለህ። ቤት ውስጥ አትታይም። መንፈሳዊ ሕይወታችን ምን ያህል ባዶ እንደሆነ አስተውለሃል? ከተጋባን ስንት ቀን እንደቈረብን ታውቃለህ? ስጠይቅህ ነገ ነገ እያልክ ጊዜውን ገደልከው። ንስሓ አባታችንን አግኝተን ንስሓ የገባነው መቼ ነው? መንፈሳዊ ሕይወታችን አያሳስብህም? ያ ሁሉ ጥንካሬህ የት ገባ?"

> "እኔንም ይቅር በለኝ" አለች ዕንባዋን እየጠረገችና ሶፋው ላይ ቁጭ እያለች። "አንቺ ምንም አላጠፋሽም፣ እኔ ነኝ ኃላፊነቴን የዘነጋሁት። ወደ ፊት በዚህ ሁኔታ መቀጠል የለብንም። መተጋገዝ አለብን። እኔ የልጆቻችንን ኃላፊነት በአግባቡ እወጣለሁ።

አክሊሉ ጥፋቱን ሲያስብ ሊሸከመው የማይችለው ጸጸት ፈጠረበት። የልጁን ጥያቄ መመለስ ተስኖት ጭራሽ የባለቤቱን፣ የግማሽ አካሉን ብሶት ቀሰቀሰ። ሐና ትክክል መሆኗን ያውቃል። ንግግራቸውን ወደ ጭቅጭቅ ሳይሆን ወደ ውይይት መውሰድ እንዳለበት ተገነዘበ። ሳሎኑ አሁንም ዝምታውን ተረከበ። አክሊሉ በኃፍረት አቀርቅሯል። ሐና ገንፍሎ የመጣውን ብሶት ያዘለ ንዴቷን ለማብረድ እና ለቅሶዋን ለማቆም ትታገላለች። ናሆምና ኤፍራታ በዝምታ ወላጆቻቸውን ይመለከታሉ። ከቆይታ በኋላ "ወደ ኋላ መመለስ አንችልም። የሆነው ሆኖ ዐልፏል። ጥፋቴን አምኛለሁ ይቅርታ። ይቅር ማለት የሚችሉ ልቦች የታደሉ ናቸው። ይቅር በይኝ ውዴ! ያለፈውን እንርሳ፣ ቤታችንን በይቅር ባይነት ደግመን እንሥራው" ብሎ በባለቤቱና በልጆቹ

መካከል በግንባሩ ተደፍቶ "ይቅር በሉኝ!" አለ፡፡

ሐና ደነገጠች፡፡ በአንድ ጊዜ እንዲህ ውስጡ ይሰበራል ብላ አላሰበችም፡፡ ባለቤቷን ትወደዋለች፤ ታከብረዋለችም፡፡ ከትምህርት ቤት ጀምሮ ማንነቱን ታውቃለች፡፡ ስላመነበት ነገር ይሞታል፡፡ ለእሷ ያለው ፍቅር ወሰን እንደሌለው ተረዳለች፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ጭልጥ ብሎ ሥራው ላይ ብቻ መጠመዱ እያሳሰባት፣ ፍርሃት እየገባት ሁሉን ተሸክማ ዛሬ ላይ ደርሳለች፡፡ ፊት ለፊቷ ተደፍቶ ይቅርታ ሲጠይቃት ንዴቷ ከላይዋ ላይ እንደ ጢስ ተነነ፡፡ አዘነችለት፡፡ የፍቅር ትኩስ ዕንባ እያነባች ከተደፋበት ብድግ አድርጋ አቀፈችው፡፡ ሁለቱም ተያይዘው ተላቀሱ፣ ልጆቹ ወላጆቻቸውን አቅፈው በዕንባ አጀቧቸው፡፡ የፍቅር፣ የጸጸት፣ የጭንቀት፣ የደስታ ዕንባ፣ ድምፅ አልባ የዕንባ ዘለላዎች ጎረፉ፡፡ "ይቅርታ አድርገሽልኛል?" አለ አክሊሉ ከእቅፏ ወጥቶ ግንባሯን በፍቅር እየሳመ፡፡

"እኔንም ይቅር በለኝ" አለች ዕንባዋን እየጠረገችና ሶፋው ላይ ቁጭ እያለች፡፡ "አንቺ ምንም አላጠፋሽም፣ እኔ ነኝ ኃላፊነቴን የዘነጋሁት፡፡ ወደ ፊት በዚህ ሁኔታ መቀጠል የለብንም፡፡ መተጋገዝ አለብን፡፡ እኔ የልጆቻችንን ኃላፊነት በአግባቡ እወጣለሁ፡፡ ተጨማሪ ኃላፊነቶች ካሉ ልትሰጪኝ ትችያለሽ፡፡ አንዳችን የአንዳችንን ጉድለት ከመሙላት ጀምሮ እየተነጋገርን እንረዳዳለን" አለ ባለቤቱን በፍቅር እየተመለከተ፡፡ እርሷም የተጠራቀመ ብሶቴን በአንድ ጊዜ አራገፍኩብህ አይደል? በቅድሚያ ትኩረት የምናደርገው መንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ ቢሆን እመርጣለሁ፡፡ እሑድ ከቅዳሴ መልስ የንስሓ አባታችንን እናነጋግራለን፡፡ እርሳቸው የሚመክሩንን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡ በጸሎት እየበረታን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት እናጠናክራለን፡፡ የልጆቻችንም፣ የቤታችንም ኃላፊነት በጋራ ብንወጣ ምን ይመስልሃል?" በማለት ባለቤቷንና ልጆቿን በፈገግታ ተመለከተቻቸው፡፡ እርሱም መልካም ነው፡፡ እስከ አሁን ብዙ ተጎድተሻልና አንዲት ረዳት ብትኖረን ደስ ይለኛል፡፡ በሥራ ደክመሽ ውለሽ እንደገና ወደ ጓዳ ማለቱ እጅግ አድካሚ ነው አለ፡፡ እርሷም አስቤው ነበር፡፡ ጥሩ ጠባይ ያላት ሠራተኛ የምናገኝ ከሆነ አጠያይቃለሁ፡፡

አክሊሉ "ልጆች እናታችሁን እናመሰግናለን! ብላችሁ ሳሚት" አለ እየሳቀ፡፡ ሁለቱም እናታቸው አንገት ላይ ተጠመጠሙ፡፡ እቅፍ አድርጋ ስትስማቸው ቆይታ "አሁን ተራው ለአባታችሁ ነው ሒዱና ሳሙት" አለቻቸው፡፡ ልጆቹ አባታቸውን አቅፈው ከሳሙት በኋላ ኤፍራታ ከአባቷ ጋር መጫወት ፈለገች፡፡ ናሆም ደግሞ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ፈለገ፡፡ ሐና ባለቤቷንና ልጆቿን በፍቅር ዓይኖች እያስተዋለች "በሉ እናንተ ተጫወቱ፡፡ እኔ እራታችንን ላዘጋጅ" ብላ ወደ ጓዳ ገባች፡፡ ከላይዋ ላይ ትልቅ ሸክም ተነሣላት፡፡ ለብዙ ጊዜ ሲያስጨንቃት የቆየው ጉዳይ ባልጠበቀችው ጊዜ መፈታቱ አስገረማት፡፡ እፎይታ በውስጧ ነገሠ፡፡ ቤቱ በአንድ ጊዜ ከዝምታ ድባብ ወደ ፍቅር ጨዋታ ተለወጠ፡፡ ቤቱ ውስጥ ሲያንዣብብ የነበረው ዳመና ተገፈፈ፡፡ ሲጫወቱ ቆይተው ናሆም ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ "የቅድሙን ጥያቄ እኮ አልመለስክልኝም" አለ፡፡

"እኔ መጫወት ነው የምፈልገው" አለች ኤፍራታ እያኮረፈች፡፡ አክሊሉ "ቆይ ለወንድምሽ አሁን ጠይቆኝ ለነበረው ጥያቄ መልስ ልስጠውና ከአንቺ ጋር እንጫወታለን አላት ዐይን ዓይኗን እየተመለከተ፡፡ ኤፍራታ እንዳኮረፈች ተቀመጠች፡፡ አክሊሉ የልጁን ምላሽ አልጠበቀም ከናሆም ጋር ጀምረውት ወደ ነበረው ጥያቄና መልስ ተሸጋገሩ፡፡ አክሊሉ ለልጁ እንዴት በቀላሉ ሊያስረዳው እንደሚችል አሰበ፡፡ ቅዱስ ዳዊት "እግዚአብሔር ያበራልኛል፣ ያድነኛልም" (መዝ.፳፮.፩) ብሏል፡፡ በብርሃንና በጨለማ እኩል አንንገዝም፣ በጨለማ ውስጥ ሆነን የምናየውን ነገር መለየት ያቅተናል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር የተሰወረውን እንደሚገልጥልን እያመንን ዓይኖቻችንን ገልጠን በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በቤታችን ሆነን እንጸልያለን፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም "የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ፣ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃንን ያገኛል እንጂ በጨለማ ውስጥ አይመላለስም" (ዮሐ.፰.፲፪) በማለት አይሁድ የሠሩትን ክፋት በጨለማ መስሎ ተናግሯል፡፡

በተጨማሪም "ሕይወት በእርሱ ነበረ፣ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረ፣ ብርሃንም በጨለማ ያበራል፣ ጨለማም አላሸነፈውም" (ዮሐ.፩፥፭) በማለት ወንጌላዊው ዮሐንስ ይነግረናል፡፡ እኛም በብርሃን ልንመላለስ ይገባል፡፡ "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ብሎ የተናገረውንና እርሱ ብርሃን ሆኖ ብርሃንነቱን የገለጠልን የአምላካችን ቃል አምነን በመቀበል እንደ ቃሉ መኖር ይኖርብናል፡፡ በዚህ ምክንያት ዓይኖቻችንን ጨፍነን አንጸልይም፡፡ አንተ በአቅምህ ማወቅ ያለብህን እንጂ ከአቅምህ በላይ እያሰብክ መጨነቅ የለብህም፡፡ ሁለታችሁም ቅዳሜ ሰንበት ትምህርት ቤት ትገባላችሁ፡፡ በየሳምንቱ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ትከታተላላችሁ" አለ አክሊሉ በትክክል መግለጹንና ልጁ የተናገረውን ይረዳ አይረዳ ለማወቅ በትኩረት እየተመለከተው፡፡

"ገብቶኛል አባዬ እኔ እኮ ሲከራከሩ አላስችልህ እያለኝ ነው" አለ፡፡"እኔ ነገ ትምህርት ቤት ሔጄ ከኃላፊዎቹ ጋር እነጋገራለሁ፡፡ በተረፈ የእናንተ ግዴታ መማር ብቻ ነው፡፡ ገና ልጆች ስለሆናችሁ ስለ ሃይማኖት መከራከር አይገባችሁም" በማለት አስጠነቀቀው፡፡ "ጥያቄዬን ስለመለስክልኝ አመሰግናለሁ፤ ያዘዝከኝንም እፈጽማለሁ" አለ ናሆም በአባቱ መልስ ተደስቶ፡፡"ራት ደርሷል፣ እጃችሁን ታጠቡ" አለች ሐና ከጓዳ ሆና፡፡ ናሆም የእጅ ውኃ አቅርቦ አስታጥቧቸው የተዘጋጀውን ማዕድ ከበው መመገብ ጀመሩ፡፡ አክሊሉ ለቤተሰቡ የነፈገውን ጊዜ በመስጠቱ፣ የልጁንና የሚስቱን ጥያቄ መመለስ በመቻሉ፣ ከሚስቱም ጋር በመወያየቱና መግባባት በመቻላቸው ተደሰተ፡፡ ✤

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

**ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን**

**በጥያቄዎቻችሁ መልስ ዓምዳችን ጳጕሜንና የዘመን መለወጫን በተመለከተ ለሚነሡ ጥያቄዎች መልስ ይሰጡን ዘንድ በማኅበረ ቅዱሳን መደበኛ አገልጋይ የሆኑትን አባ ዐሥራተ ማርያም ደስታን ጋብዘናል። መልካም ንባብ።**

**ሐመር፡-** አባታችን የምናነሣቸው ጥያቄዎች ከጳጕሜንና ከዘመን መለወጫ ጋር የተያያዙ ናቸው። ለመሆኑ ጳጕሜን ማለት ምን ማለት ነው?



**አባ ዐሥራተ ማርያም ደስታ**

**አባ ዐሥራተ ማርያም፡-** ጳጕሜን ማለት ቃሉ የጽርዕ ወይም የግሪክ ሲሆን ኤፓጎሜን ማለት ነው። ትርጓሜውም ጭማሪ ማለት ነው። በግእዝ ተውሳክ ይባላል። በሌላ አገላለጽ ከዐውደ ወርኅ ስለተረፈና በዓመት መጨረሻ ስለተገኘ ተረፈ ዓመት ይባላል። በዓመተ ዑደተ ፀሐይ አንድ ዓመት ፫፻፷፭ ቀናት ነው። ይህን ለ፴ ስናካፍለው ፲፪ ይደርስና ፭ ይቀራል። እነዚህ ፭ ቀናት ጳጕሜን ተብለው ስለሚጠሩ ጳጕሜን ማለት ጭማሪ ወይም ተረፈ ዓመት ተብሎ ይጠራል።

**ሐመር፡-** አባታችን የጳጕሜን ሥስቱ ዓመታት አምስት፣ አምስት ቀናት ሆነው ሲውሉ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ደግሞ ስድስት ቀን ይሆናል። ምክንያቱን ቢያብራሩልን?

**አባ ዐሥራተ ማርያም፡-** ይህ የሚሆንበት ምክንያት ከእያንዳንዱ ዓመት ተጨማሪ ስድስት ስድስት ሰዓት ትርፍ በመኖሩ ነው። በየዓመቱ የተረፈው ስድስት ሰዓት በዐራተኛው ዓመት ፳፬ ሰዓት ሞልቶ አንድ ቀን ይሆናል። በዘመነ ሉቃስ ጳጕሜን ስድስት የሚሆነው በየዓመቱ የተረፉት ስድስት ስድስት ሰዓታት ተደምረው አንድ ቀን ስለሚሞሉ ነው።

**ሐመር፡- በጳጕሜን ወር ክርስቲያኖች የመጠመቃቸው ምክንያት ምንድ ነው?**

**አባ ዐሥራተ ማርያም፡-** ምክንያቱን በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው ከኢዮብ ጋር ተያይዞ ሲተላለፍ የመጣ ነው። ኢዮብ በደዌ ሥጋ በተመታ ጊዜ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ከደዌው ተፈወሰ፤ አዲስ ማንነትንም አገኘ። ዛሬም ሰዎች በዚያ ልማድ አምስቱን ወይም ስድስቱን ዕለታት በአካባቢያቸው ወደ ሚገኘው ወንዝ እየሔዱ ይጠመቃሉ። አዲሱን ዓመት በአዲስ መንፈስ ለመቀበል ሲሉ የሚያደርጉት ነው። ታሪካዊ አመጣጡ ኢዮብን መሠረት ያደረገ ነው።

ሁለተኛው ግን ከጳጕሜን ወር ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁለት ዐበይት ነገሮችን ልብ ማለት ያስፈልጋል። እነርሱም አንደኛው ርኅወተ ሰማይ ሲሆን፣ ሁለተኛው የሊቀ መልአኩ የቅዱስ ሩፋኤል ዓመታዊ በዓል ነው። ርኅወተ ሰማይ ማለት የሰማይ መከፈት ማለት ነው። እንዲህ የተባለው በሰማይ መከፈት መዘጋት ኑሮበት አይደለም። እስጢፋኖስ የእግዚአብሔርን ክብር ባየ ጊዜ ሰማይ ተከፍቶ አየሁ በማለት እንደተናገረው ዓይነት ነው። በሐዋርያት ሥራ "በእስጢፋኖስም ላይ መንፈስ ቅዱስ መላ፤ ወደ ሰማይም ተመለከተ፤ የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ። እነሆ ሰማይ ተከፍቶ የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ" (ሐዋ.፯፥፶፭-፶፮) ተብሎ እንደተጻፈ የማይታይና የማይገለጥ ምሥጢር ተገልጦ ሲታይ ሰማይ ተከፈተ ተባለ። እንደዚሁ ሁሉ የእግዚአብሔር ምሕረት ቸርነት ወደ ሰው፣ የሰው ጸሎት ልመና ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ መሆኑን የሚያመለክት ነው። የመልአኩ የቅዱስ ሩፋኤልን ዓመታዊ በዓልም የምናከብረው በዚህ ወር ማለትም በጳጕሜን ፫ ነው። በዚህ ዕለት የቅዱስ ሩፋኤል በዓለ ሢመት ነው። እንዲሁም በዚህ ዕለት የጸለይነውን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያደርስልናልና እናከብረዋለን።

በዚህ ዕለት ዝናም የዘነመ እንደሆን ሰዎች ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ እንፈወሳለን ብለው ስለሚያምኑ ይጠመቃሉ። አስቀድሞ እንደተገለጸው ርኅወተ ሰማይ ማለት የሰው ጸሎት ልመና ወደ እግዚአብሔር ሲደርስ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ምሕረት፣ ፈውስ ወደ ሰው ይደርሳል። ሰው የሚጠመቀውም ለመፈወስ ነው። ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ ቸርነት ለማግኘት ማለት ነው። ስለዚህ በዚህ በጳጕሜን ወር የሚደረገው ጥምቀት በቅዱስ ሩፋኤል ስም በፈለቀ ጠበል የሚደረግ ጥምቀት ማለት ነው።

**ሐመር፡- ጳጕሜንን በዚህ መልኩ ከተመለከትን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዕንቊጣጣሽም አለና ምንነቱን ቢያስረዱን?**

**አባ ዐሥራተ ማርያም፡-** ዕንቊጣጣሽ የሚለው ቃል የተለያየ ትርጕም አለው፤ የተወሰነውን ለመጥቀስ ያህል፡- አበባ፣ ዕንቊዕ፣

ዕፅ አወጣሽ፣ ዕንቍዕ ዕጣ ወጣሽ፣ ዕንቁ ለጣጣሽ ማለት ነው፡፡ ለምን እንዲህ እንደተባለ ዘርዘር አድርጎ እያንዳንዱን ማየት ስለሚያስፈልግ ከላይ በተጠቀሱበት ቅደም ተከተል እንመለከት፡-

**ሀ.ዕንቍጣጣሽ፡- አበባ ማለት ነው፡፡** ዕንቍጣጣሽ አበባ የሚባለው እንደሚታወቀው ይህ ወቅት አበባ የሚፈነዳበት ነው፡፡ አበባ ለፍቅር፣ ለደስታ መግለጫ ስጦታ ሆኖ ስለሚሰጥ ለአዲስ ዓመትም ስጦታ መስጠት የተለመደ ነው፡፡ በአዲስ ዓመት ልጃገረዶች ለታላላቅ ሰዎች የሚሰጡት ስጦታ አበባ ሲሆን ዕንቍጣጣሽ ሰጡን ይባላሉ፡፡ ያልሰጡትንም ዕንቍጣጣሽ ሰጠሽ? እየተባባሉ ይጠያየቃሉ፡፡ በሚሰጡበትም ጊዜ ዕንቍጣጣሽ በማለት ይሰጣሉ፡፡ አበባ እነሆ እንደማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዕንቍጣጣሽ ማለት አንደኛው ትርጕም አበባ ማለት ነው፡፡

በአዲስ ዓመት ልጃገረዶች ለታላላቅ ሰዎች የሚሰጡት ስጦታ አበባ ሲሆን ዕንቍጣጣሽ ሰጡን ይባላሉ። ያልሰጡትንም ዕንቍጣጣሽ ሰጠሽ? እየተባባሉ ይጠያየቃሉ። በሚሰጡበትም ጊዜ ዕንቍጣጣሽ በማለት ይሰጣሉ። አበባ እነሆ እንደማለት ነው።

**ለ. ዕንቍጣጣሽ፡- ዕንቍዕ ዕፅ አወጣሽ፡-** ሁለተኛው ትርጕም ዕንቍዕ ዕፅ አወጣሽ ማለት ሲሆን ከኖኅ ዘመን ክሥተት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ኖኅ የወረደውን የጥፋት ውኃ በመርከብ ሆኖ ካለፈው በኋላ እየቀነሰ ሲሔድ መርከቧም ከአራራት ተራራ ላይ ዐርፋ ነበርና መሥዋዕት ሠውቶ፣ መጉደል አለመጉደሉን ለማወቅ አስቀድሞ ቁራን ላከው፡፡ በዚያው ሳይመለስ ቀረ፡፡ ዛሬ በሀገራችን የቁራ መልክተኛ የሚባለው አነጋገር ከዚያ ጋር የተያይዘ ነው፡፡ ርግብን ሲልካት ፍሬ ያለው አበባ "ቆጽለ ዕፀ ዘይት" ይዛ መጣች፤ የወይራ ቅጠል ማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ኖኅ ውኃው እንደጎደለ ስለተረዳ ከመርከብ ወጣ፡፡ ምድር ለምልማ፣ አጊጣና አምሮባት ሲያገኛት "ዕንቍዕ ዕፅ አወጣሽ" በማለት ተናገረ፡፡ እኛም ዛሬ ክረምቱ አልፎ ምድር ለምልማ፣ በአበባ አጊጣና አምሮባት የምትታይበት ወቅት ስለሆነ ዕንቁጣጣሽ እንላለን፡፡

**ሐ. ዕንቍ ዕጣ ወጣሽ ማለት ነው፡-** ይህም ከኖኅ ልጆች ጋር የተያያዘ ታሪክ አለው፡፡ ታሪኩም ኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ በመልአኩ ዳኝነት በዕጣ ርስት ሲያከፋፍላቸው ለካም አፍሪካ ደረሰውና የካም ልጅ ኩሽ ወደ ኢትዮጵያ መጣ፡፡ ኢትዮጵያን ሲያገኛት እጅግ የለመለመች መልካም ሀገር ሆና አገኛት፡፡ በዚህ ጊዜ "ዕንቍ ዕጣ ወጣሽ" በማለት ደስታውን ገለጸ፡፡

**መ. ዕንቍዕ ለጣጣሽ ማለት ነው፡፡** የመጨረሻው ከንግሥተ ሳባ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ንግሥተ ሰባ የሰሎሞንን ዝና ሰምታ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ይዛ ወደ ኢየሩሳሌም ሔደች፡፡ እርሷ ወደ ኢየሩሳሌም ሔዳ ንጉሥ ሰሎሞንን ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ጠይቃ የጠየቀቻቸውም ጥያቄዎች ተመልሰውላት እንደተመለሰች በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ፲÷፩-ፍጻሜ የተጻፈ ሲሆን በታሪክ መዝገብ ተጽፎ ባይገኝም አባቶች በትውፊት የሚናገሩት ታሪክ አለ፡፡ እርሱም ከሰሎሞን ጋር ተገናኝታ፣ ለእርሱ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን አበርክታ፣ እንቀቅልሿ ተፈቶላትና ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳ ስትመለስ እርሱም በፊንታው "ዕንቁ ለጣጣሽ፣ ለቤትሽ ጣጣ ይሁንሽ" ብሎ ዕንቍዕ ሰጥቶ ሰደዳት፡፡ ስለዚህ ዕንቍዕ ለጣጣሽ ማለት ነው ተብሎ ይተረካል፡፡

**ሐመር፡-** አባታችን ዕንቍጣጣሽ አንዳንዴ የዘመን መለወጫ እየተባለም ይጠራልና ትክክለኛው ስያሜ ይህ ነው ማለት ይቻላል? ከተቻለ ቢገልጹልን፡፡

**አባ ዐሥራተ ማርያም፡-** በአጠቃላይ ዕንቍጣጣሽ ማለት ከላይ የዘረዘርናቸውን ትርጕሞች የሚይዝ ሲሆን በስያሜ ደረጃ አዲስ ዓመት፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ርእሰ ዐውደ ዓመት ወዘተ. እየተባለ ይጠራል፡፡ የስያሜው ጉዳይ ሳይሆን ለምን እንደዚህ ተብሎ ይጠራል የሚለው ነው መታየት ያለበት፡፡

ርእሰ ዓውደ ዓመት የተባለው በዘመን መለወጫ የሚውል የመጀመሪያው ዓመታዊ በዓል ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህ ሊቁ ቅዱስ ያሬድም "ርእሰ ዐውደ ዓመት ዮሐንስ ወላዴ መጥቅዕ ወአበቅቴ፣ መጥቅዕንና አበቅቴን የሚወልድ የዐውደ ዓመት ሁሉ ራስ ዮሐንስ" ብሎ ገለጸው፡፡ በዚህ ዕለት መገበሪያ፣ ወይን፣ ዕጣን ወዘተ ቀርቦ ጸሎተ ዕጣን ይደገማል፤ ሊቃውንቱ ባሕረ ሐሳብ ያወጣሉ፤ በባሕረ ሐሳብ የሚወጡት የዓመቱ በዓላትና አጽዋማት ተሰልተው ይታወጃሉ፡፡ ስለዚህ ርእሰ ዐውደ ዓመት ተብሎ ይጠራል፡፡ የበዓላትና የአጽዋማት ራስ መገለጫ፣ መታወቂያ ማለት ነው፡፡

ሌላኛው ስያሜ ቅዱስ ዮሐንስ ነው፡፡ ይህ ስያሜ የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ምትረተ ርእስ መስከረም ሁለት ስለሚታሰብ ከዚህ ጋር አያይዞ ለመግለጽ ነው፡፡ ምትረተ ርእሱን ለማስታወስ ቅዱስ ዮሐንስ "ዋርሳ አትውረሱ" እያለ ሲያስተምር ሄሮድስንም "የወንድምንህን የፊልጶስን ሚስት ታገባ ዘንድ አይገባህም" በማለት ስለገሠጸው አስሮት ነበርና የልደት በዓሉን

በሚያከብርበት ጊዜ የሄሮድያዳ ልጅ በዘፈን አስደሰተችው። በዚህ ጊዜ ከደስታው ጽናት የተነሣ የለመንሽኝን ሁሉ አደርግልሻለሁ አላት። እናቷን ብታማክር የዮሐንስን ራስ ቆርጦ ይስጥሽ አለቻት። በዚህ ጊዜ እንቢ እንዳይላት የገባው ቃል አስጨነቀው። እሺ እንዳይላት ዮሐንስን እንደ ነቢይ ይቈጥሩት ነበርና ሕዝቡን ፈራ። ይሁን እንጂ "ሕዝቡን በጦር እታገለዋለሁ" ብሎ የዮሐንስን ራስ አስቆርጦ ሰጣት። ይህ የሆነበት መስከረም ሁለት ቀን ስለሆነ በዓሉን ከዚያ ጋር አያይዞ ለማክበር አዲሱን ዘመን ቅዱስ ዮሐንስ ብለን እንጠራዋለን።

ከላይ የተገለጸው አንደኛው ምክንያት ሲሆን በዋናነት ግን ቅዱስ ዮሐንስ ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት ቅዱስ ዮሐንስ መንገድ ጠራጊ ይባላል። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት ከስድስት ወር አስቀድሞ የሰበከ፣ እኔ የጫማውን ማሰሪያ እፈታ ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በፊት የነበረው ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ነው። "እኔ ለንስሓ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን ለመሸከም የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል" (ማቴ.፫÷፲፩) እያለ ያስተማረ የሐዲስ ኪዳንን መምጣት የነገረ ነቢይ ወሐዋርያ ነው። እርሱ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ድልድይ ነው። ስለዚህ አበው ከአሮጌው ዘመን ወደ ሐዲሱ ዘመን የምንሸጋገርበትን ዘመን በቅዱስ ዮሐንስ ሰይመውታል። ቅዱስ ዮሐንስ ከብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ እንደሆነ ሁሉ በቅዱስ ዮሐንስ የተሰየመው የእኛም አዲስ ዓመት ከክረምት ወደ መፀው የምንሸጋገርበት ነው። ስለዚህ የሐዲሱ ዓመትና የአሮጌው ዓመት መሸጋገሪያ ቅዱስ ዮሐንስ ይባላል።

**ሐመር፡-** **አባታችን ስያሜው ከአራቱ ወንጌላውያን አንዱ በሆነው በቅዱስ ዮሐንስ የተሰየመ ነው ብለው የሚናገሩ ሰዎች ስላሉ ይህን ቢያብራሩልን?**

**አባ ዐሥራተ ማርያም፡-** አራቱ ወንጌላውያን ዘመኑን ለአራት ተከፋፍለው እየተፈራረቁ ምግብናቸውን ያከናውናሉ። በየራሳቸው ዘመነ ማቴዎስ፣ ዘመነ ማርቆስ፣ ዘመነ ሉቃስና ዘመነ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል። ከስያሜያቸውም በወንጌልም አጉልተው ከጻፉት አንጻር የየራሳቸው ምሳሌ አላቸው። ማቴዎስ በገጸ ሰብእ፣ ማርቆስ በገጸ አንበሳ፣ ሉቃስ በገጸ ላሕም፣ ዮሐንስ በገጸ ንስር ይመሰላሉ። የአዲስ ዓመት ስያሜ ቅዱስ ዮሐንስ ተብሎ የሚጠራው በመጥምቁ ዮሐንስ እንጂ በወንጌላው ዮሐንስ አይደለም። አስቀድሞ እንደተገለጸው መጥምቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን እና የሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ድልድይ ነውና የዘመኑም ስያሜ ክረምት ዐልፎ በጋው የሚተካበት ስለሆነ አሮጌው ዘመን አልፎ ሐዲሱን ዘመን የምንቀበልበት ዓመታዊ በዓል በመጥምቁ ዮሐንስ ተሰይሟል።

**ሐመር፡-** አባታችን የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ለምን በመስከረም ሆነ? ለምን እንደሌሎች በጥር ወይም በሌላ ወር አልሆነም?

እንግዲህ በመጽሐፍ እንደሚታወቀው እስራኤላውያን ከግብፅ ከ፬፻፴ የመከራ ዘመናት በኋላ ወጥተው፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት፣ በሙሴ መሪነት ባሕር ተከፍሎላቸው፣ ጠላት ተገድሎላቸው ሲወጡ ነፃ የወጡበትን ዕለት የአዲስ ዓመት መለወጫ አድርገውታል። ወሩም ሚያዝያ ነው። ከመከራ የወጣንበት ነው፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን የተሸጋገርንበት ነው ለማለት ነው።

እንደዚህ ሁሉ የእኛም አዲስ ዓመት በረከታቸው ይድረሰንና የቀደሙ አባቶቻችን እንዳስተማሩን የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ በመስከረም የሆነበትን ምክንያት፤ ክረምት የመከራ፣ የጨለማና የስቃይ ምሳሌ ነው። ስለዚህ ከዚህ መከራ የምንሸጋገርበትን፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን የምንወጣበትን ወቅት አዲስ ዓመት ብለን እናከብራለን በማለት ያስረዳሉ። ደግሞም ከላይም እንደተገለጸው መስከረም ማለት ምስየተ ክረምት፣ የክረምት መካተቻ፣ ማለት ነውና ክረምቱ ዐልፎ ምድር በአበባ የምታሸበርቅበት ወቅት ሲመጣ አዲስ ዓመት እናከብራለን። ቅዱስ ያሬድም "ኀለፈ ክረምት ቆመ በረከት ተሠርገወት ምድር በሥነ ጽጌያት፣ ክረምት ዐለፈ፤ በረከት ተተካ፤ ምድርም በአበቦች አጌጠች" ብሎ እንደገለጸው ምድር የምትፈካበት፣ በአበቦች የምታጌጥበት፣ እውነትም አዲስ ዘመን የምናይበት ነውና በዚህ ወቅት ተደርጓል።

አዲስ ዓመት ማለት አዲስ ነገር ስናይ ነውና በውኃ ተሸፍና የነበረችው ምድር ውኃዋ ጎድሎላት፣ ዕፅዋቱ ለምልመው አብበው፣ አሸብርቀው ለምድር ጌጥ ሆነው፣ ሙላቱ፣ ጨለማው፣ ጭቃው፣ መከራው ዐልፎ በአበባ ያሸበረቀች ምድር፣ በዕፅዋት ልምላሜ የፈካች ምድር የምናይበት ነው። ከላይ እንደተገለጸው ኖኅ በውኃ ተሸፍና የነበረችው ምድር ውኃው ጎድሎላት በልምላሜ አጊጣ፣ አብባ ሲመለከታት ዕንቍ ዕፅ አወጣሽ እንዳላት እኛም በውኃ ሙላት ስትናጥ የነበረችው ምድር በልምላሜ፣ በአበባ ወዘተ. አጊጣ ስንመለከት እነዚህን አበቦች እያየን የምንደሰትበት ወቅት ነውና በዚህ ወቅት አዲስ ዓመት ብለን እናከብራለን።

**ሐመር፡-** አባታችን ጊዜዎን ሰጥተው ለጥያቄዎቻችን ተገቢ የሆነውን መልስ ስለሰጡን እግዚአብሐሔር ያክብርልን፤ የአገልግሎት ዘመንዎን ይባርክልን፤ ቃለ ሕይወት ያሰማልን።

**አባ ዐሥራት፡-** አሜን!! እናንተንም እግዚአብሔር ይባርክላችሁ። ማኅበሩን ይጠብቅልን። ⌖